# Ss

*S, s* (ኤስ)
አስራ ዘጠነኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*sack* (ሳክ)
1. ጆንያ/ ትልቅና ጠንካራ ከረጢት/
The man put the potatoes into a sack.
ሰውየው ድንቾቹን በጆንያ ውስጥ ከተታቸው።



2. ከስራ ማባረር
He got the sack because he was always late for work.
ሁልጊዜ አርፍዶ ስራ ስለሚገባ ከስራው ተባረረ።

*sad* (ሳድ)
ያዘነ/ደስተኛ ያልሆነ/
We were sad when the old man died.
ሽማግሌው ሲሞቱ አዝነን ነበር።



*saddle* (ሳድል)
ኮርቻ/ ፈረስ ላይ ለመጋለብ ፈረሱ ጀርባ ላይ የሚደረግ መቀመጫ
The man bought a new saddle for the horse.
ሰውየው ለፈረሱ አዲስ ኮርቻ ገዛለት።



*safe* (ሴይፍ)
1. ካዝና/በጣም ከባድ የሆነ የብረት ሳጥን ውድ የሆኑ ነገሮችንና ገንዘብ ማስቀመጫ/
The lady kept her money in the safe.
ሴትየዋ ገንዘቧን ካዝና ውስጥ አስቀመጠች።
2. አደጋ የሌለበት/የማያስፈራ/
If you stay in the house you will be safe.
እቤት ብትቀመጥ ምንም አደጋ አያጋጥምህም።

*sail* (ሴይል)
1. በወንዝ ወይም በባሕር ላይ መጓዝ
It will take us two days to sail across the lake.
ሀይቁን ለማቋረጥ ሁለት ቀን ይፈጅብናል።



2. የመርከብ ሸራ/በመርከብ ላይ የሚታሰር ጨርቅ
The sails filled with wind and the ship began to move quickly.
የመርከብ ሸራው በንፋስ በመሞላቱ መርከቡ በፍጥነት መጓዝ ጀመረ።

*sailor* ('ሴይለ)
መርከበኛ/መርከብ ላይ የሚሰራ ሰው
There are one hundred sailors on that ship.
መርከቧ ላይ አንድ መቶ መርከበኞች አሉ።



***saint*** (ሴይንት)
ቅዱስ/ በጣም ጥሩ ሰው
He looks after the poor children. He is a saint.
የተቸገሩ ህፃናትን ይረዳል በጣም ጥሩ ሰው ነው።

***salad*** ('ሳለድ)
ሰላጣ/ጥሬ ከሆኑ ቅጠላቅጠሎች የሚሰራ ምግብ/
My mother prepared salad for lunch.
እናቴ ለምሳ ሰላጣ አዘጋጀች።

***salt*** (ሶ:ልት)
ጨው
I put salt and pepper on the table.
ጨውና በርበሬ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩ።

*same* (ሴይም)
እኩል/አንድ አይነት/
My twin sister and I are the same age.
መንትያ እህቴና እኔ እድሜያችን እኩል ነው።

*sand* (ሳንድ)
አሸዋ/በጣም የደቀቀ ድንጋይ/
The boy is playing with sand.
ልጁ በአሸዋ እየተጫወተ ነው።



*sandal* ('ሳንድል)
ነጠላ ጫማ/ዙሪያው ክፍት የሆነ ጫማ/
Sandals are cool in hot weather.
ነጠላ ጫማዎች በሙቀት ጊዜ ይቀዘቅዛሉ።



*sandwich* ('ሳንዊጅ)
ሳንዱች/ተከፍሎ መሀሉ ላይ ስጋ፣ እንቁላል ተከቶበት የሚበላ ዳቦ
My brother like s to eat

sandwiches.
ወንድሜ ሳንድዊች መብላት ይወዳል።



*sardine* (ሳ:ዲ:ን)
ሰርዲን/ ትንንሽ አሳ/ሚጠጢጠ. አሳ
Sardines are usually sold in tins.
ሰርዲኖች ብዙ ጊዜ በቆርቆሮ ታሽገው ይሸጣሉ።



*Saturday* ('ሳተዴይ)
ቅዳሜ/የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን/
We do not go to school on Saturday.
ቅዳሜ ወደ ት/ቤት አንሄድም።

*sauce* (ሶ:ስ)
ስጎ/ከፓስታ፣ መኮረኒ ወይም ሩዝ ጋር የሚበላ ወጥ/
This cheese sauce is very good with rice.
ይህ የአይብ ስጎ ከሩዝ ጋር በጣም ጥሩ ነው።

*saucepan* ('ሶ:ስፓን)
ባለ እጀታ ብረት ድስት
She cooked the porridge in the saucepan.
ገንፎውን በባለ እጅታ ብረት ድስት አበሰለችው።

*save* (ሴይቭ)
1. ያለውን ሁሉ ሳያጠፉ ለሌላ ጊዜ ማስቀመጥ/መቆጠብ
I am saving my money to buy a radio.
ሬዲዮ ለመግዛት ገንዘቤን እየቆጠብኩ ነው።
2. ከአደጋ /ከችግር/ ማዳን
He saved her from the car accident.
ከመኪና /አደጋ/ አዳናት።

*saw* (ሶ:)
መጋዝ/የእንጨት የብረት መቁረጫ ባለጥርስ ብረት/
Melaku cut the tree down with his saw.
መላኩ ዛፉን በመጋዙ ቆረጠው።



*say* (ሴይ)
መናገር/አንድ ነገር ማለት
He says that he did not take her book.
መፅሀፏን አልወሰድኩም ይላል።

*scales* (ስኬይልዝ)
ሚዛን/የአንድን ነገር ክብደት ለመለካት

የሚያገለግል መሳሪያ/
Use the scales to weigh the meat.
ስጋውን ለመመዘን ሚዛን ተጠቀም።



*scar* (ስካ፡)
ጠባሳ/ጉንዲጎ/አንድ ቁስል ከዳነ በኋላ ሰውነት ላይ የሚቀር ምልክት/
He has a scar on his arm where the dog bit him.
ውሻው የነከሰው እጁ ላይ ጠባሳ አለበት።


*scare* (ስኬየ)
አስደነገጠ/ተደናገጠ
The cat was so scared it ran up a tree.
ድመቷ በጣም ስለደነገጠች ዛፍ ላይ ወጣች።

*school* (ስኩ፡ል)
ትምህርት ቤት/ ልጆች ትምህርት የሚማሩበት ቤት
My sister is starting to go to school today.
እህቴ ዛሬ ትምህርት ቤት መሄድ ትጀምራለች።



*science* (ሳይየንስ)
ሳይንስ
I want to be a science student.
የሳይንስ ተማሪ መሆን እፈልጋለሁ።

*scissors* ('ሲዘዝ)
መቀስ/ ልብስ፣ ወረቀት መቁረጫ/
My mother used her scissors to cut my hair.
እናቴ ፀጉሬን ለመከርከም መቀሷን ተጠቀመች።



*scold* (ስከውልድ)
በቁጣ መናገር/መገሰፅ
The teacher scolded us for making a noise.
አስተማሪው ስለጮህን ገሰፀን።

*scooter* ('ስኩ፡ተ)
ትንሽ ሞተር ሳይክል
When you are on a scooter always wear your helmet.
በትንሽ ሞተር ሳይክል በምትሄድበት


ጊዜ ሁልጊዜ የራስ መከላከያ
ኮፍያህን አድርግ።



*scrub* (ስክረብ)
ቆሻሻ መጥረግ ማፅዳት
I will scrub the kitchen floor. It is very dirty.
የማዕድቤቱን ወለል አፀዳዋለሁ በጣም ቆሻሻ ነው።

*sea* (ሲ:)
ባህር/ሰፊ ቦታ ላይ የተጠራቀመ ውሃ/
You cannot drink sea water.
የባህር ውሀ መጠጣት አትችልም።

*seal* (ሲ:ል)
ሲል/አሳ በሊታ የባህር እንስሳ
Seals eat fish.
ሲሎች አሳ ይበላሉ።



*seat* (ሲ:ት)
መቀመጫ
My father made a seat out of the log.
አባቴ ከጉቶው መቀመጫ ሰራ።



*second* ('ሴከንድ)
1. ሴኮንድ/የሰአት መቁጠሪያ ትንሹ መለኪያ/
Sixty seconds make one minute.
ስልሳ ሴኮንዶች አንድ ደቂቃ ይሆናሉ።
2. ሁለተኛ
Fitsum came second in the English exam.
ፍፁም በእንግሊዝኛ ፈተና ሁለተኛ ወጣ።

*secret* ('ሲ:ክረት)
ምስጢር/ሌላ ሰው የማያየው ወይም የማይሰማው ድብቅ ነገር/
The money is hidden in a secret place.
ገንዘቡ በምስጢራዊ ቦታ ተደብቋል።

*see* (ሲ:)
በአይን ማየት
Can you see that aeroplane in the sky?
ያንን በሰማይ ላይ ያለውን አይሮፕላን ማየት ትችላለህ?

*seed* (ሲ:ድ)
ዘር/እንዲበቅል የሚዘራ እህል/
The farmer is sowing his corn seeds.
ገበሬው የበቆሎ ዘሮቹን እየዘራ ነው።



*seem* (ሲ:ም)
እንድ ነገር የሆነ መምሰል
The cat seems to be asleep. Its eyes are closed.
ድመቱ የተኛ ይመስላል አይኖቹ ተጨፍነዋል።

*sell* (ሴል)
መሸጥ/ አንድን ነገር በገንዘብ መለወጥ
My mother sells eggs in the market.
እናቴ እንቁላሎች ገበያ ውስጥ ትሸጣለች።

*send* (ሴንድ)
መላክ/ አንድ ነገር ለሌላ ሰው እንዲያደርሱ መስጠት
Please send me a letter when you go to Awasa.
አዋሳ ስትሄድ እባክህ ደብዳቤ ላክልኝ።

*sense* (ሴንስ)
የስሜት ህዋስ/መዳሰስ፣ መስማት፣ ማሽተት፣ መዳበስ፣ መቅመስ
There are five senses.
አምስት የስሜት ሕዋሣት አሉ።

*sensible* ('ሴንስብል)
ተገቢ የሆነ ነገር/ ድርጊት
It is sensible to wear a warm coat when it is cold.
በብርድ ጊዜ የሚሞቅ ኮት መልበስ ተገቢ ነው።

*sentence* (ሴንተንስ)
አረፍተ-ነገር/ ቃላት ተቀጣጥለው የሚፈጥሩት ትርጉም
A sentence ends with a full stop.
አረፍተ ነገር በአራት ነጥብ ያልቃል።

*September* (ሴፕቴምበ)
መስከረም/ በጎርጎሮሣውያን የዓመቱ 9ኛ ወር በኢትዮጵያዊያን የዓመቱ 1ኛ ወር/
My father starts his new job in September.
አባቴ አዲሱን ስራውን በመስከረም ይጀምራል።

*serious* ('ሲየሪየስ)
1. ከበድ ያለ/ ጠንከር ያለ
My uncle had a serious car crash.
አጎቴ ከባድ የመኪና አደጋ ደርሶበታል።
2. ቀልድ ያልሆነ/ጠንከር ያለ ንግግር
The teacher is going to have a serious talk with you.
አስተማሪዋ ካንተ ጋር ጠንከር ያለ ንግግር ልታደርግ ነው።

*set* (ሴት)
1. አንድ ላይ ሊሆኑ የሚችሉ የነገሮች ወይም የሰዎች ስብስብ
My brother bought a set of encyclopedias yesterday .
ትላንትና ወንድሜ የእውቀ ጥበብ ስብስቦችን ገዛ።
2. ፀሃይ ስትጠልቅ
We will be home before the sun sets.

ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት እቤት እንመለሳለን።



***seven*** (።ሴ·ቨን)
ሰባት/7/
There are seven days in a week.
በሳምንት ውስጥ ሰባት ቀናት አሉ።

***seventeen*** (ሴቨን·ቲ፡ን)
አስራ ሰባት/17/
My sister is seventeen years old.
እህቴ አስራ ሰባት አመት ነው።

***seventy*** ('ሴቨንቲ)
ሰባ/70/
The bus will hold seventy people.
አውቶቡሱ ሰባ ሰው ይይዛል።

***sew*** (ሰው)
መስፋት/የተቀደደን ነገር በክር ማያያዝ/
Please sew the button on my shirt.
እባክህን ሸሚዜ ላይ ቁልፉን ስፋልኝ።

***shadow*** (ሻዶው)
ያንድ ሰው/ያንድ ነገር ጥላ
You can see her shadow when she is standing in front of the light.
ከብርሀን ፊት ለፊት ስትቆም ጥላዋን ልታይ ትችላለህ።



***shake*** (ሼይክ)
1. መወዝወዝ/መነቅነቅ
Shake the bottle before you take a drink.
ከመጠጣትህ በፊት ጠርሙሱን ነቅንቀው።
2. መጨባበጥ/ ለሰላምታ እጅና እጅን ማገናኘት
Do you always shake hands when you meet your friend?
ሁልጊዜ ከጓደኛህ ጋር ስትገናኙ ትጨባበጣላችሁ?



***shall*** (ሸል)
የወደፊት ድርጊትን መግለጫ ነገር
I shall leave home at two o'clock.
ከቤት በሁለት ሰአት እወጣለሁ።

***shallow*** ('ሻለው)
ጥልቀት የሌለው ውሀ
You can swim. The water is shallow.
ውሀው ጥልቀት ስለሌለው መዋኘት ትችላለህ።

*shape* (ሼይፕ)
የአንድ ነገር የውጭኛው ቅርፅ
A ball has round shape.
ኳስ ክብ ቅርጽ አለው።



*share* (ሼየ)
ማካፈል/ አንድን ነገር ለሁሉም መስጠት/
Tiringo shared her sweets with the other boys.
ትርንጎ ከረሜላዎቿን ከሌሎች ልጆች ጋር ተካፈለች።

*shark* (ሻ:ክ)
ሻርክ/ ረጃጅም ጥርሶች ያሉት ትልቅ አሳ/
Sharks will attack people who are swimming in the sea.
ሻርኮች በባህር ውስጥ የሚዋኙ ሰዎችን ሊያጠቁ ይችላሉ።



*sharp* (ሻ:ፕ)
ስለታም በጣም የሾለ
The sharp knife cut his finger.
ስለታሙ ቢላ እጁን ቆረጠው።



*shed* (ሼድ)
የዛፍ ወይም የትልቅ ነገር ጥላ
My father keeps his tools in the shed.
አባቴ የእጅ መሳሪያዎቹን ጥላ ስር ያስቀምጣል።

*sheep* (ሺ:ፕ)
በግ/ ሥጋው ለምግብነት የሚያገለግል የቤት እንስሳ
A young sheep is called a lamb.
ትንሽ በግ ጠቦት ይባላል።



*sheet* (ሺ:ት)
አንሶላ/የአልጋ ምንጣፍ
I have pink sheets on my bed.
አልጋዬ ላይ ሀምራዊ አንሶላ ተነጥፏል።

*shelf* (ሼልፍ)
የመፅሃፍ/የዕቃ መደርደሪያ
Put those books back on the shelf.
እነዚያን መፅሀፎች ወደ መፅሃፍ መደርደሪያው ላይ መልሳቸው።



*shell* (ሼል)
ጠንካራ ሽፋን/የእንቊላል /የቀንድ
አውጣ
Snails and some other animals have shells.
ቀንድ አውጣዎችና አንዳንድ እንስሳዎች
ጠንካራ ሽፋን አላቸው።



*shepherd* (ሼፐድ)
እረኛ/በግ ወይም ከብት ጠባቂ
The shepherd led the flock of sheep up the hill.
እረኛው የበጉን መንጋ ወደ
ተራራው ነዳ።

*shin* (ሺን)
መሀል አገዳ ቅልጥም/ከጉልበትና
ከእግር በላይ ያለ ቦታ/
My brother hurt his shin playing football.
ወንድሜ እግርኳስ ሲጫወት ቅልጥሙ
ተጎዳ።

*shine* (ሻይን)
ማብራት/ ማብረቅረቅ
The sun shines during the day.
ፀሀይ ቀን ቀን ታበራለች።

*ship* (ሺፕ)
መርከብ/በባሕር ላይ የሚጓዝ/
A ship can carry many people.
መርከብ ብዙ ሰው ሊይዝ ይችላል።



*shirt* (ሸ፡ት)
ሸሚዝ
Tariku was wearing a red shirt and a tie.
ታሪኩ ቀይ ሸሚዝና ክረባት አድርጎ
ነበር።



*shiver* (ሺቨ)
የሰውነት መወዛወዝ/መንቀጥቀጥ/
በብርድ ወይም በፍርሃት
When the antelope saw the lion it shivered with fright.
ድኩላው አንበሳውን ባየ ጊዜ በፍርሀት
ተንቀጠቀጠ።

*shock* (ሾክ)
መደንገጥ
We got a shock when we saw that our car was gone.
መኪናችን እንደተወሰደ ባየን ጊዜ
ደነገጥን።

*shoe* (ሹ:)
ጫማ
I have a pair of red shoes.
ቀይ ጥንድ ጫማ አለኝ።



*shoot* (ሹ:ት)
ጠመንጃ/ሽጉጥ ተኩሶ መግደል
Give him the money or he will shoot you.
ገንዘቡን ስጠው አለበለዚያ ይገድልሀል።

*shop* (ሾፕ)
ሱቅ/እቃ መሸጫ ቤት
We have a big grocer's shop in our village.
በመንደራችን ትልቅ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ አለ።

*shopkeeper* (ሾፕ ኪ:ፐ)
ሱቅ ውስጥ የሚሰራ ወይም ባለሱቅ
Shopkeepers work in a shop.
ባለሱቆች ሱቅ ውስጥ ይሰራሉ።



*short* (ሾ:ት)
አጭር
It's a short walk to my house.
እቤቴ ድረስ ያለው ርቀት አጭር ነው።

*shorts* (ሾ: ትስ)
ቁምጣ/አጭር ሱሪ/ከጉልበት በላይ የሚቀር
Shorts are good for sporting activities.
ቁምጣዎች ለስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ጥሩ ናቸው።




*shoulder* (ሾውልደ)
ትከሻ
The men carried the poles on their shoulders.
ሰዎቹ ምሰሶዎቹን በትከሻቸው ተሸከሟቸው።

*shout* (ሻውት)
መጮኽ/ድምፅን ከፍ አድርጎ መናገር/
The policeman shouted at the boys to get off the road.
ፖሊሱ ልጆቹ መንገዱን እንዲለቁ ጮኾ ነገራቸው።

*show* (ሸው)
ማሳየት
I am going to show you my new dress.
አዲሱን ቀሚሴን ላሳይህ ነው።


*shower* (ሻወ)
1. ካፊያ/ለስላሳ ዝናብ
It is only a shower. Let us go.
እንሂድ ይህ ካፊያ ብቻ ነው።

2. የቁም ገላ መታጠቢያ
I take a shower every morning.
ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ገላዬን እታጠባለሁ።



***shrink*** (ሽሪንክ)
መጨማደድ
Do not wash those trousers in hot water. They will shrink.
እነዚያን ሱሪዎች በሙቅ ውሃ እንዳታጥባቸው ይጨማደዳሉ።

***shut*** (ሸት)
መዝጋት
Please shut the window or the goats will get out.
እባክህ መስኮቱን ዝጋው አለበለዚያ ፍየሎቹ ይወጣሉ።



***shy*** (ሻይ)
ድንጉጥ/ሰውን ማየት የሚፈራ/አይን አፋር
The little girl is shy.
ትንሿ ልጅ አይን አፋር ናት።

***sick*** (ሲክ)
በሽተኛ/ህመምተኛ/ህመም
My mother put me to bed as I was feeling sick.
የህመም ስሜት ሲሰማኝ እናቴ አልጋ ላይ አስተኛችኝ።



***side*** (ሳይድ)
1. ጎን
Put that box down on its side.
ያንን ሳጥን በጎኑ አስቀምጠው።
2. ወገን ወይም ቡድን
Are you playing football for the red side or the green side?
ለቀይ ወገን ነው ወይስ ለአረንጓዴ እግር ኳስ የምትጫወተው?

***sight*** (ሳይት)
ማየት/ በአይን የማየት ችሎታ
The old man lost his sight.
ሽማግሌው የማየት ችሎታቸውን አጡ።

***sign*** (ሳይን)
1. አቅጣጫ ወይም ስነስርአት ማሳያ ምልክቶች
A driver must always follow the traffic signs.
ሹፌር ሁልጊዜ የመንገድ ምልክቶችን

መከተል አለበት።




2. ፊርማ መፈረም
Your mother did not sign this letter.
እናትህ እዚህ ደብዳቤ ላይ አልፈረመችም።

*silent* (ሳይለንት)
ፀጥ ያለ/ምንም ድምፅ የማይሰማበት/
The library was silent. There was no noise.
ቤተመፃህፍቱ ፀጥ ብሏል ምንም ድምፅ አይሰማም።

*silly* ('ሲሊ)
ጥሩ ያልሆነ/የማይረባ
She is a silly girl. She lost her purse.
እሷ የማትረባ ልጅ ናት ቦርሳዋን ጣለችው።

*silver* ('ሲልቨ)
ብር/ ለጌጥነት የሚያገለግል ነጭ ብረት
She is wearing a beautiful silver brooch.
እሷ በጣም የተዋበ ከብር የተሰራ የአንገት ጌጥ አድርጋለች።

*simple* ('ሲምፕል)
ቀላል/ ለመስራት የማያስቸግር
What's two and two? That's a simple question.
ሁለትና ሁለት ስንት ነው? ያ በጣም ቀላል ጥያቄ ነው።

*since* (ሲንስ)
ከአንድ ከተወሰነ ጊዜ ጀምሮ
I have not seen Daro since Friday.
ከአርብ ጀምሮ ዳሮን አላየሁትም።

*sing* (ሲን)
መዝፈን/ መዘመር/ ዜማ ባለው ድምፅ መናገር/
Please sing me one of your lovely songs.
እባክህ ከጣፋጭ ዘፈኖችህ አንዱን ዝፈንልኝ።




*single* ('ሲንግል)
1. ነጠላ/አንድ ብቻውን/
He has not scored a single goal.
አንድም ግብ አላገባም።
2. ያላገባ ወንድ ወይም ያላገባች ሴት/ ላጤ/
She is single, but her brother is married.
እሷ ላጤ ነች ወንድሟ ግን አግብቷል።

*sink* (ሲንክ)
1. ውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ

መግባት/ መስመጥ
That ship is going to sink in the sea.
ያ መርከብ ባሀሩ ውስጥ ሊሰምጥ ነው።
2. ቁም ዕቃ ማጠቢያ ሳፋ
My mother washed my shirt in the sink.
እናቴ ሸሚዜን በቁም ሣፋው ላይ አጠበችልኝ።

*sister* (ሲስተ)
እህት
My sister is younger than I am.
እህቴ የእኔ ታናሽ ናት።

*sit* (ሲት)
መቀመጥ
You sit on the chair. I will sit on the bed.
እናንተ ወንበር ላይ ተቀመጡ። እኔ አልጋው ላይ እቀመጣለሁ።




*six* (ሲክስ)
ስድስት/6/
I have six brothers and one sister.
ስድስት ወንድሞችና አንድ እህት አለኝ።

*sixteen* (ሲክስ'ቲ፡ን)
አስራ ስድስት/16/
My uncle is coming to see us in sixteen days.
አጎቴ በአስራ ስድስት ቀን ውስጥ ሊያየን ይመጣል።

*sixty* (ሲክስቲ)
ስልሳ/60/
There are sixty days in two months.
በሁለት ወራት 60 ቀናት አሉ።

*size* (ሳይዝ)
ቁጥር/የአንድ ነገር መጠን ስፋት/
My shoes are size six.
የጫማዬ ስፋት ስድስት ቁጥር ነው።

*skeleton* ('ስኬሊትን)
/አፅም/ሰው ከሞተ በኋላ ስጋው ፈርሶ የሚቀረው አጥንት
Those bones are the skeleton of a man.
እነዛ አጥንቶች የሰው አፅሞች ናቸው።



*skin* (ስኪን)
ቆዳ/ለአትክልት ልጣጭ/እንስሳት የተሸፈኑበት የላይኛው አካል
An apple has a smooth skin.
አፕል ለስላሳ ልጣጭ አለው።

***skip*** (ስኪፕ)
**መቦረቅ/በደስታ መጨፈር መጫወት/**
I love to play and skip with my friends.
**ከጓደኞቼ ጋር መጫወትና መቦረቅ እወዳለሁ።**

***skirt*** (ስከ፡ት)
**ጉርድ ቀሚስ/ከወገብ በታች የሆነ የሴቶች ልብስ/**
The teacher is wearing a long skirt today.
**አስተማሪዋ ዛሬ ረጅም ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች።**

***sky*** (ስካይ)
**ሰማይ**
You can see lots of stars in the sky at night.
**በምሽት ብዙ ኮከቦችን በሰማይ ላይ ታያለህ።**

***slap*** ('ስላፕ)
**በጥፊ መምታት**
My mother slapped me because I broke the window.
**መስኮቱን ስለሰበርኩ እናቴ በጥፊ መታችኝ።**

***sleep*** (ስሊ፡ፕ)
**እንቅልፍ መተኛት**
Babies need a lot of sleep.
**ህፃናት ብዙ እንቅልፍ ያስፈልጋቸዋል።**



***sleeve*** (ስሊ፡ቭ)
**እጅጌ/እጅን የሚሸፍነው የሸሚዝ ወይም የኮት ክፍል**
He rolled up his sleeves to keep them clean.
**ልብሱ እንዳይቆሽሽ እጅጌውን ወደላይ ሰበሰበ።**



***slice*** (ስላይስ)
**ቁራጭ ወይም ቁራሽ**
Please give me a slice of bread.
**እባክህ ቁራሽ ዳቦ ስጠኝ።**



***slide*** (ስላይድ)
**መንሸራተት/ሳይራመዱ ከፍ ካለ ነገር ላይ ወደታች መውረድ**
The boys slid on the slide.
**ልጆቹ በሸርተቴው/በመንሸራተቻው ላይ ተንሸራተቱ።**



***slip*** (ስሊፕ)
እየተንተቱ እየተሳቡ መሄድ
The donkey slipped on the wet path up the hill.
አህያው በጨቀየው መንገድ ወደ ኮረብታው እየተንተተ ሄደ።

***slope*** (ስለውፕ)
ቁልቁለት ወይም ዳገት
We can not ride our bicycles up the steep slope.
በብስክሌታችን ወደ ዳገቱ መጋለብ አንችልም።



***slow*** (ስለው)
ቀርፋፋ/በጣም ቀስ ብሎ የሚሄድ/
The train is so slow that we are going to be late.
ባቡሩ በጣም ቀርፋፋ ስለሆነ ሳንዘገይ አንቀርም።

***slowly*** (ስለውሊ)
በዝግታ ቀስ ብሎ
When you get old you start walking slowly.
በምታረጅበት ወቅት በዝግታ መሄድ ትጀምራለህ።

***smack*** (ስማክ)
በጥፊ መምታት/ በመዳፍ መምታት
The cruel man smacked the boy on the head many times.
ጨካኙ ሰው ልጁን ጭንቅላቱ ላይ ደጋግሞ መታው።

***small*** (ስሞ፡ል)
ትንሽ
The puppy is very small to jump over the wall.
ቡችላው በአጥር ላይ ለመዝለል በጣም ትንሽ ነው።

***smart*** (ስማ፡ት)
በጣም የሚያምር/ጥሩ
You are wearing a very smart hat.
1. በጣም የሚያምር ኮፍያ አድርገሀል።
2. ጉበዝ/አዋቂ/ንቁ
She is the smartest student in her class.
እሷ በክፍሏ ውስጥ ካሉት ሁሉ ጉበዝ ናት።

***smash*** (ስማሽ)
ተጋጭቶ መሰበር
The jar hit the floor and smashed into pieces.
ገንቦው መሬት ላይ ወድቆ ተሰባበረ።



***smell*** (ስሜል)
ማሽተት/የማሽተት ሀይል
I can smell the food from here.
ምግቡን ከዚህጋ ማሽተት እችላለሁ።

***smile*** (ስማይል)
ፈገግታ/ፈገግ ማለት/

The baby smiled when it saw its mother.
ህፃኑ እናቱን ሲያይ ፈገግ አለ።

*smoke* (ስሞውክ)
**ጭስ/አንድ ነገር ነዶ እሳቱ ሲጠፋ የሚወጣ ጠቆር ወይም ነጣ ያለ አየር/**
The smoke floated up into the sky.
**ጭሱ ወደሰማይ ወጣ።**



***smooth*** (ስሙ:ዝ)
**ለስላሳ/ የማይሻክር**
Glass is smooth.
**መስታወት ለስላሳ ነው።**

***snail*** (ስኔይል)
**ቀንድ አውጣ**
Snails live inside their shell.
**ቀንድ አውጣዎች በጠንካራ ቅርፊታቸው ውስጥ ይኖራሉ።**



***snake*** (ስኔይክ)
**እባብ/በደረቱ የሚሳብ ገመድ ቀበቶ የመሰለ እንስሣ**
Some snakes are poisonous.
**አንዳንድ እባቦች መርዛማ ናቸው።**



*snap* (ስናፕ)
**መንከስ**
The cat snapped his finger.
**ድመቷ ጣቱን ነከሰችው።**

*snatch* (ስናች)
**መንጠቅ/ሌላ ሰው የያዘውን ነገር በግድ መውሰድ/**
He snatched my bag and ran away.
**ቦርሳዬን ነጥቆኝ ሮጠ።**

***sneeze*** (ስኒ:ዝ)
**ማስነጠስ**
This dust made me sneeze.
**ይህ አቧራ አስነጠሰኝ።**

*snore* (ስኖ:)
**ማንኮራፋት/ሲተኙ ድምፅ እያሰሙ መተንፈስ/**
I hope you don't snore.
**እንደማታንኮራፉ ተስፋ አደርጋለሁ።**

*snow* (ስነው)
**ከሰማይ የሚወርድ ጥጥ የሚመስል በረዶ**
Snow falls from the sky when it is very cold.
**ሀይለኛ ቅዝቃዜ ሲኖር በረዶ ከሰማይ ይወርዳል።**

***snug*** (ስነግ)
**መመቸት**
I am snug in my soft bed.

በማይቀረቀረው አልጋ ውስጥ ተመችቶኛል።

*soak* (ሰውክ)
ውሀ በውሀ አደረገ/አበሰበሰ
That heavy rain will soak your clothe.
ያ ከባድ ዝናብ ልብስህን ያበሰብሰዋል።

*soap* (ሰውፕ)
ሳሙና/የቆሸሹ ነገሮችን ማጠቢያ
I need more soap to finish washing the clothes.
ልብሶቹን አጥቤ ለመጨረስ ተጨማሪ ሳሙና እፈልጋለሁ።

*sob* (ሰብ)
መንሰቅሰቅ/በሃይል ማልቀስ
The little girl sobbed when she lost her ball.
ኳሷ ስትጠፋባት ትንሿ ልጅ እየተንሰቀሰቀች አለቀሰች።

*soccer* (ሶከ)
እግር ኳስ/ የእግር ኳስ ቡድን
There is a soccer match this afternoon.
ዛሬ ከሰአት በኋላ የእግር ኳስ ግጥሚያ አለ።



*sock* (ሶክ)
ካልሲ/የእግር ሹራብ/
Our mother told us to put on our shoes and socks.
ካልሲያችንንና ጫማችንን እንድናደርግ እናታችን ነገረችን።



*social* ('ሰውሸል)
ማህበራዊ/ከሰዎች ጋር በህብረት
Man is a social animal.
ሠው ማህበራዊ እንስሣ ነው።

*sofa* ('ሰውፈ)
ሶፋ/ ምቾት ያለው ባለመደገፊያ ወንበር
Three people can sit on our sofa.
ሶፋችን ላይ ሶስት ሰዎች መቀመጥ ይችላሉ።



*soft* (ሶፍት)
ለስላሳ የሆነ ነገር
Pillows are soft.
ትራሶች ለስላሳ ናቸው።

*soil* (ሶይል)
አፈር
That soil needs a lot of water

before we plant the beans.
ባቄላውን ከመትከላችን በፊት አፈሩ ብዙ ውሀ ያስፈልገዋል።

*soldier* ('ሰውልጀ)
ወታደር/ስራው አገር/ወገን/መጠበቅ የሆነ ሰው/
The soldier is carrying his gun.
ወታደሩ ጠመንጃውን ይዟል።



*some* (ሰም)
ጥቂት/ብዙ ያልሆነ/
There are some fruits on the table.
ጥቂት ፍራፍሬዎች ጠረጴዛው ላይ አሉ።

*someone* ('ሰምወን)
አንድ ያላየነው/የሆነ ሰው
Someone knocked at the door.
የሆነ ሰው በር አንኳኳ።

*sometimes* ('ሰምታይም)
አንዳንድ ጊዜ
Sometimes I walk from office to home.
አንዳንድ ጊዜ ከቢሮ ወደ ቤት በእግሬ እሄዳለሁ።

*son* (ሰን)
ወንድ ልጅ
I have five sons and two daughters.
አምስት ወንድ ልጆችና ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ።



*song* (ሶን)
ዘፈን
The girls sang a song.
ሴቶቹ ልጆች ዘፈን ዘፈኑ።

*soon* (ሱ:ን)
በቅርብ ጊዜ/ቶሎ
The bus will be coming soon.
አውቶቡሱ ቶሎ ይመጣል።

*sore* (ሶ:)
የታመመ የሰውነት ክፍል
My legs are sore after playing football.
እግር ኳስ ከተጫወትኩ በኋላ እግሬን ያመኛል።


*sorry* ('ሶሪ)
ላጠፉት ጥፋት ይቅርታ መጠየቅ/ ማዘንን መግለፅ
The police felt sorry for arresting me by mistake.
ፖሊሶቹ በስህተት ስላሠሩኝ አዘኑ።

*sort* (ሶ:ት)
የእቃው/የነገሩ አይነት
What sort of car does your father have?
አባትህ ምን አይነት መኪና ነው ያለው?


*sound* (ሳውንድ)
በጆሮ የሚሰማ ድምፅ
Can you hear the sound of the train coming?
በመምጣት ላይ ያለው የባቡር ድምጽ ይሰማሀል?

*sour* (ሳው)
መራራ /የሚጎመዝዝ/ የማይጣፍጥ
I cannot drink this milk. It is sour.
ይህንን ወተት መጠጣት አልቻልኩም ይመራል።

*south* (ሳውዝ)
የደቡብ አቅጣጫ
Kenya is south of Ethiopia.
ኬንያ ከኢትዮጵያ በስተደቡብ ትገኛለች።




*sow* (ሰው)
1. ሴት አሳማ
The sow had fourteen little pigs.
አሳማዋ አስራ አራት ግልገሎች አሏት።



2. መዝራት
I am going to sow wheat and beans this year.
በዚህ አመት ስንዴና ባቄላ እዘራለሁ።

*space* (ስፔይስ)
1. ባዶ ቦታ/ ምንም የሌለበት
You can park the car in that empty space.
መኪናውን እዛ ባዶ ቦታ ላይ ማቆም ትችላለህ።
2. ህዋ/ሰማይ/
There are many stars in space.
በህዋ ውስጥ ብዙ ከዋክብት አሉ።

*spade* (ስፔይድ)
አካፋ አፈር መዛቂያ መሳሪያ
The gardener has a big spade.
አትክልተኛው ትልቅ አካፋ አለው።



*spark* (ስፓ፡ክ)
የእሳት ፍንጣቂ
A spark flew out of the fire and burnt a hole in the rug.
ከእሳቱ ፍንጣቂ መጥቶ ምንጣፉን አቃጠሎ በሳው።

*speak* (ስፒ፡ክ)
መናገር/ አንድን ነገር ለሰው መንገር
My mother will speak to my father about the holiday.
እናቴ ስለአመት በአሉ ለአባቴ ትነግረዋለች።

*speed* (ስፒ:ድ)
**ፍጥነት**
The police car went down the road at a high speed.
**የፖሊስ መኪናው በከፍተኛ ፍጥነት በመንገዱ ቁልቁል ወረደ።**


*spell* (ስፔል)
**አንድ ቃል የተፃፈባቸው ፊደላት**
Can you spell your name?
**ስምህን መፃፍ ትችላለህ?**

*spend* (ስፔንድ)
**አንድን ነገር ለመግዛት ገንዘብ ማውጣት**
How much did you spend on food this week?
**በዚህ ሳምንት ለምግብህ ምን ያህል አወጣህ?**

*spider* (ስፓይደ)
**ሸረሪት/በየቤቱ ግድግዳ ላይ የምትገኝ እግር ያላት ድር የምትሰራ ነፍሳት/**
Most spiders make webs to catch flies.
**አብዛኞቹ ሸረሪቶች ዝንቦችን ለመያዝ ድር ያደራሉ።**



*spill* (ስፒል)
**ማፍሰስ ወይም መድፋት**
The boy spilt the milk on the floor.
**ልጁ ወተቱን ወለሉ ላይ ደፋው።**



*spin* (ስፒን)
**በክብ መዞር መሽከርከር**
I was spinning so fast, so I felt dizzy.
**በፍጥነት ስሽከረከር ጭው አለብኝ።**

*spit* (ስፒት)
**ምራቅን መትፋት**
Zebiba was spitting angrily at muhe.
**ዘቢባ በቁጣ ሙሄ ላይ ስትተፋበት ነበር።**

*splash* (ስፕላሽ)
**ውሃ ማንቦራጨቅ/መርጨት**
When the boy jumped into the river he splashed us.
**ልጁ ወደ ወንዙ ዘሎ ሲገባ አንቦራጨቀብን።**



*split* (ስፕሊት)
**መፍለጥ/ለሁለት መሰንጠቅ**
The man split the log with his axe.
**ሰውየው ግንዲላውን በመጥረቢያው ፈለጠው።**

*spoil* (ስፖይል)
ማቆሸሽ/ማበላሸት
Keep your hands clean not to spoil your dress.
ልብስሽን እንዳታበላሺው እጅሽን በንፅህና ጠብቂ።

*sponge* (ስፓንጅ)
1. በባሕር ውስጥ የሚኖር የማይንቀሳቀስ እሳ/ሰፍነግ/
Sponges have a lot of holes in them to soak up water.
ሰፍነጎች ውሀ ለመምጠጥ የሚያገለግሏቸው ብዙ ቀዳዳዎች አሏቸው።
2. ስፖንጅ/ እቃን ወይም ገላን ለማጠብ የሚያገለግል ለስላሳ ነገር
Use a soap and sponge to wash your body.
ገላህን ለመታጠብ ሳሙናና ስፖንጅ ተጠቀም።

*spoon* (ስፑ፡ን)
ማንኪያ/የሻይ፣ የቡና የመሳሰሉትን ማማስያ ብረት/
Spoons can be made of metal or wood.
ማንኪያዎች ከብረት ወይም ከእንጨት ሊሠሩ ይችላሉ።



*sport* (ስፖ፡ት)
ስፖርት
Football, volleyball and tennis are all sports.
እግር ኳስ፣ መረብኳስና ቴኒስ ሁሉም ስፖርት ናቸው።



*spot* (ስፖት)
1. ነቁጥ/ክብ ምልክት ነጥብ
My sister has a dress with red spots.
እህቴ ቀይ ነጠብጣቦች ያሉት ቀሚስ አላት።
2. ለይቶ ማየት/ ማነጣጠር
The hunter spotted the leopard lying in the grass.
አዳኙ በሳር ላይ የተኛውን አቦሸማኔ አነጣጥሮ አየው።

*spring* (ስፕሪንግ)
1. ፀደይ/ከክረምት በኋላ ያለ የአበባ ወራት
New leaves appear on the trees in spring.
በፀደይ ዛፎች አዲስ ቅጠል ያበቅላሉ።
2. ምንጭ/ከመሬት የሚፈልቅ ውሃ
Spring water is good to drink.
የምንጭ ውሃ ለመጠጥ ጥሩ ነው።
3. ዘለለ/መዝለል/መንጠር
The cat sprang up and caught the bird.

ድምጹ ዘሎ ወፏን ያዛት።
4. የሚያነጥር ጥምዝ ሽቦ (ለአልጋ/ለወንበር)
Don't jump on the bed the springs are not strong.
አልጋው ላይ አትዝለል የሚያነጥሩት ሽቦዎች ጠንካራ አይደሉም።

*square* (ስክዌየ)
እኩል የሆኑ 4 ጎኖች ያሉት ነገር/አራት ማዕዘን ቅርጽ
Can you find a square box to put the books in?
መፅሀፎቹን የምታስቀምጥበት አራት ማዕዘን ሳጥን ማግኘት ትችላለህ?



*squeak* (ስክዊ:ክ)
ሲጥ ሲጥ የሚል ድምፅ የአይጥ አይነት
The mouse squeaked when it saw the corn.
አይጧ በቆሎውን ስታይ ሲጥ ሲጥ አለች።

*squeeze* (ስክዊ:ዝ)
መጭመቅ/አንድን ነገር ጨምዶ መያዝ
We squeezed the oranges to make juice.
ጭማቂ ለመስራት ብርቱካኖቹን ጨመቅናቸው።

*squirrel* ('ስክዊረል)
ሽኮኮ
Squirrels have thick furry tails.
ሽኮኮዎች ወፍራምና በጉራማ ጅራት አላቸው።



*stable* ('ስቴይብል)
የፈረስ ጋጣ/ፈረሶች የሚያድሩበት ቤት/
There are six horses in the stable.
በጋጣው ውስጥ ስድስት ፈረሶች አሉ።

*stain* (ስቴይን)
የውሃ ወይም የፈሳሽ ጠብታ
The ink has left a stain on the cloth.
የቀለሙ ጠብታ በጨርቁ ላይ ቀረ።

*stair* (ስቴየ)
ወደ ፎቅ ቤት መውጫ መንገድ/ደረጃ/
Go up those stairs to the bedroom.
ወደ መኝታ ቤቱ በነዚያ ደረጃዎች ውጣ።



*stamp* (ስታምፕ)
ቴምብር/ዶብዳቤ ሲፃፍ ፖስታው ላይ የሚለጠፍ የተለያዩ ስዕሎች ያሉት ትንሽ ወረቀት
You buy stamps and put them on the envelops.

ቴምብሮች ገዝተህ ፖስታዎቹ ላይ ለጥፍ።



*stand* (ስታንድ)
1. አንድ ቦታ መቆም
We will stand under the tree until the rain stops.
ዝናቡ እስኪያባራ ዛፉ ስር እንቆማለን።
2. የአንድ ነገር ማስቀመጫ
Put the cake stand in the middle of the table.
የኬኩን ማስቀመጫ ጠረጴዛው መሀል ላይ አድርገው።

*star* (ስታ፡)
ኮከብ/ማታ ማታ በሰማይ ላይ የሚያበሩ ጥቃቅን ነገሮች
The stars look like diamonds in the night sky.
ከዋክብቶቹ በምሽት ሰማይ ላይ አልማዞች ይመስላሉ።



*stare* (ስቴየ)
አይንን ማፍጠጥ
She stared at the boy who bit the dog.
ውሻውን የመታው ልጅ ላይ አፈጠጠችበት።

*start* (ስታ፡ት)
አንድ ነገር መጀመር
I will start the race when you are all ready.
ሁላችሁም ስትዘጋጁ ውድድሩን እጀምራለሁ።

*station* (ስቴይሽን)
1. ማቢያ/ተራ ባቡር፣ አውቶቡስ የሚቆምበት ቦታ
I will wait for the train at the station.
ባቡር ጣቢያው ሄጄ ባቡሩን እጠብቃለሁ።
2. ፖሊስ ጣቢያ/ፖሊሶች የሚሰሩበት ቦታ/
They took the thief to the police station.
ሌባውን ወደፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት።

*stay* (ስቴይ)
አንድ ቦታ መቆየት
My father is staying at work tonight.
አባቴ ዛሬ ማታ ስራ ይቆያል።

*steal* (ስቲ፡ል)
መስረቅ/የሌላ ሰው የሆነን ነገር ተደብቆ መውሰድ
That cat is going to steal the fish.
ድመቷ አሳውን ልትሰርቅ ነው።

*steam* (ስቲ፡ም)
እንፋሎት/ፈሳሽ/ውሃ ብዙ እሳት ላይ ሲቆይ የሚወጣ አየር/
Be careful! That steam will burn

you.
ተጠንቀቅ! ያ እንፋሎት ያቃጥልሀል።

*steep* (ስቲ፡ፕ)
1. ቀጥ ያለ ገደል ወይም ዳገት
2. ደረጃ/ ወደ ፎቅ ወይም ወደ ተራራ መውጫ/
We cannot climb the hill. It is too steep.
ኮረብታውን መውጣት አንችልም። በጣም ቀጥ ያለ ገደል ነው።

*step* (ስቴፕ)
1. ደረጃ/ወደፎቅ ወይም ወደተራራ መውጫ
Where do these steps lead to?
እነዚህ ደረጃዎች ወዴት ነው የሚወስዱት?



2. አንድን ነገር ተራምዶ ማለፍ
Step over the dog or he will bite you.
በውሻው ላይ ተራምደህ እለፍ አለበለዚያ ይነክስሀል።

*stew* (ስትዩ)
ወጥ/ከእንጀራ ወይም ከዳቦ ጋር የሚበላ/
My brother is making stew today.
ዛሬ ወጥ የሚሠራው ወንድሜ ነው።

*stick* (ስቲክ)
1. ጭራሮ/ቀጭን እንጨት/
I need some sticks to light the fire.
እሳቱን ለማቀጣጠያ ጥቂት ጭራሮ እፈልጋለሁ።



2. አንድን ነገር ሌላ ነገር ላይ መለጠፍ
Will you stick the stamp on the envelope?
ቴምብሩን ፖስታው ላይ ትለጥፈዋለህ።



*still* (ስቲል)
1. በድንጋጤ ሳይንቀሳቀሱ መቆም
The bird stood still as it watched the frog.
ወፏ እንቁራሪቷን ስታይ በድንጋጤ ቆማ ቀረች።
2. እስካሁን
Are you still here?
እስካሁን እዚህ ነህ?

*sting* (ስቲንግ)
ንብ/ተርብ ሲወጋ/ሲነድፍ/

A wasp sting is very sore.
የተርብ ንድፊያ በጣም የሚያሳምም ነው።

*stitch* (ስቲች)
የተቀደደን ነገር መስፋት
I am lcarning to stitch with a needle.
በመርፌ መስፋት እየተማርኩ ነው።

*stomach* (ስተመክ)
ሆድ/ከደረት በታች ከወገብ በላይ ያለ ሰውነት/
I ate too much. I have a pain in my stomach.
በጣም ብዙ በላሁ። ሆዴን አሞኛል።



*stone* ('ስተውን)
ድንጋይ
Don't throw stones. You may hit some body.
ድንጋይ አትወርውሩ ሰው ልትመቱ ትችላላችሁ።



*stool* (ስቱ:ል)
በርጩማ/ እጭር ባለ ሶስት እግር መቀመጫ
My mother enjoys sitting on a stool.
እናቴ በርጩማ ላይ መቀመጥ ያስደስታታል።

*stop* (ስቶፕ)
መንቀሳቀስ ማቆም
The bus always stops at our house.
አውቶቡሱ እቤታችን አጠገብ ሁልጊዜ ይቆማል።

*store* ('ስቶ:)
መደብር/መሸጫና መለወጫ ቦታ/
My mother bought bread at the food store.
እናቴ ከምግብ መደብሩ ዳቦ ገዛች።

*storm* (ስቶ:ም)
አውሎ ነፋስ
Two houses were damaged in the bad storm.
በሀይለኛው አውሎ ነፋስ ሁለት ቤቶች ፈረሱ።



*story* ('ስቶ:ሪ)
ተረት/ታሪክ
Our father tells us a story every night.
አባታችን ማታ ማታ ሁሌ ተረት

ይነግረናል።

*stove* (ስቶውቭ)
ምድጃ
The stove made the room very warm.
ምድጃው ክፍሉን በጣም አሞቀው።



*straight* (ስትሬይት)
ቀጥ ያለ
This is the straight road to the village.
ወደ መንደሩ የሚወስደው ቀጥተኛ መንገድ ይህ ነው።

*strange* (ስትሬይንጅ)
እንግዳ ነገር/ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ ቦታ
I went to a strange place to visit.
ወደ አንድ አይቼው ወደ ማላውቀው ቦታ ለጉብኝት ሄድኩ።

*stranger*(ስትሬይንጀ)
ያልታወቀ/ ዕንግዳ ሰው
What is the name of the stranger?
የእንግዳው ሰው ስም ማነው?

*stream* (ስትሪ:ም)
ትንሽ ወንዝ/ድሉሉ
Small streams flew into the river.
ትንንሽ ድሉሉዎች ወደ ወንዙ ፈሰሱ።



*street* (ስትሪ:ት)
ጉዳና/የመኪና/ የእግረኛ መንገድ
We don't live in a street.
በመንገድ ላይ አንኖርም።



*stretch*(ስትሬች)
መዘርጋት
The cat stretched her body.
ድመቷ ሰውነቷን ወጣጠረችው።



*string* ('ስትሪግ)
በጣም ቀጭን ገመድ/ክር ወይም ሲባጎ
My sister tied my birthday present with red string.
እህቴ የልደቴን ስጦታ በቀይ ክር አሠረችው።



*stripe* (ስትራይፕ)
አንድ ነገር ላይ የተሰመረ መስመር/ ሰንበር/
Zebras have black and white stripes.
የሜዳ አህዮች ጥቁርና ነጭ መስመሮች አሏቸው።



*stroke* (ስትረውክ)
ማሻሸት
I like to stroke my kitten.
የድመት ግልገሌን ማሻሸት እወዳለሁ።

*strong* (ስትሮግ)
ጠንካራ
Elephants are very strong. They can lift trees.
ዝሆኖች በጣም ጠንካሮች ናቸው ዛፎችን ማንሳት ይችላሉ።

*student* ('ስትዩ፡ድንት)
ተማሪ
My sister is a student at a secondary school.
እህቴ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ነች።



*study* ('ስ-ተዲ)
ጥናት /ማጥናት
My mother always tells me to study my lessons.
እናቴ ሁልጊዜ ትምህርቴን እንዳጠና ትነግረኛለች።

*stupid* ('ስትዩ፡ፒድ)
ደደብ/ምንም ነገር የማይገባው ሰው/
He is stupid. He cannot add fifteen and eighteen.
እሱ ደደብ ነው። አስራ አምስትና አስራ ስምንትን መደመር አይችልም።

*sty* (ስታይ)
ያሳማ ቤት
Ten pigs live in that sty.
በአሳማው ቤት አስር አሳሞች ይኖራሉ።

*subject* ('ሰብጀክት) ሱ-
የሚጠና ትምህርት
I love science subjects.
የሳይንስ ትምህርቶችን እወዳለሁ።

*submarine* (ሰብመ'ሪ:ን)
በውሃ ውስጥ የሚሄድ መርከብ
That submarine went round the world underwater.
ያ መርከብ በውሃ ውስጥ አለምን ዞረ።



*subtract* (ሰብ'ትራክት)
መቀነስ
If you subtract four from ten the answer will be six.
ከአስር ላይ አራትን ስትቀንስ መልሱ ስድስት ይሆናል።

$$10-4 = 6$$

*suddenly* ('ሰደ·ንሊ)
ወዲያውኑ/ድንገት
While I was walking in the road, suddenly I saw a car.
በመንገድ እየሄድኩ ድንገት መኪና አየሁ።

*sugar* ('ሹገ)
ስኳር/ከሸንኮራ የሚሰራ ጣፋጭ
I don't like tea without sugar.
ስኳር የሌለው ሻይ አልወድም።

*suitcase* (ሱ፡ትኬይስ)
ሻንጣ/ልብስ እና አንዳንድ ነገሮችን መያዣ
My mother is packing the suitcase. We are going to visit my grandmother.
እናቴ ሻንጣውን እያዘጋጀች ነው። አያቴን ለመጠየቅ ልንሄድ ነው።



*sum* (ሰም)
ድምር/አንድን ቁጥር ሌላ ቁጥር ላይ መጨመር
The Sum of three and thirteen is sixteen.
የሦስት እና የአስራ ሦስት ድምር አስራ ስድስት ነው።

*summer* ('ሰመ)
በጋ/በጣም ሃይለኛ ፀሃይ ያለባቸው ወራት
I like to swim in the river in summer.
በበጋ ወቅት ወንዝ ውስጥ መዋኘት እወዳለሁ።

*sun* (ሰን)
ፀሀይ
There are lots of clouds. You cannot see the sun.
ደመናው ተከምሯል። ፀሀይዋን ማየት አትችልም።



***Sunday*** ('ሰንዴይ)
እሁድ/ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን/
I always stay in bed on Sunday morning.
ሁልጊዜ እሁድ ጠዋት ተኝቼ አረፍዳለሁ።

*supper* ('ሰፐ)
መክሰስ/ እራት/ ማታ የሚበላ ምግብ
I like to eat bread and butter for supper.
መክሰስ ላይ ዳቦ በቅቤ መብላት እወዳለሁ።

*sure* (ሹወ)
ለአንድ ነገር እርግጠኛ መሆን
I'm sure I put the bottle in the box.
ጠርሙሱን ሳጥን ውስጥ እንዳስቀመጥኩ እርግጠኛ ነኝ።

*surprise* (ሰ'ፕራይዝ)
ሳያስቡት የሚደረግ አስደሳች ነገር
My birthday party was a lovely surprise.
የልደቴ ድግስ ያላሰብኩት አስደሳች ነገር ነበር።

*swallow* (ስዎለው)
መዋጥ/አንድን ነገር ወደ ሆድ ማስገባት/
Always chew your food well before you swallow it.
ሁልጊዜ ምግብህን ከመዋጥህ በፊት በደንብ አኝከው።

*swan* (ስዎ:ን)
የውሀ ዶሮ/ዳክዬ የምትመስል/
Look! There is a swan and her babies in the river.
ተመልከት! የውሃ ዶሮና ልጆቿ ወንዙ ውስጥ አሉ።



*sweater* ('ስዌተ)
ሹራብ/ ከክር የሚሰራ ከወገብ በላይ የሚለበስ ልብስ
My sister loves to wear sweaters.
እህቴ ሹራብ መልበስ ትወዳለች።



*sweep* (ስዊ:ፕ)
መጥረግ
Don't sweep the ground while we are sitting.
እኛ ተቀምጠን ሳለን ወለሉን አትጥረግ!

*sweet* (ስዊ:ት)
ጣፋጭ
My father says sweets are bad for your teeth.
አባቴ ጣፋጭ ነገሮች ለጥርስህ መጥፎ ናቸው ይላል።

*swim* (ስዊም)
ዋና/በውሃ ላይ የመንሳፈፍ ችሎታ
The boys are learning to swim in the river.
ልጆቹ ወንዝ ውስጥ መዋኘት እየተማሩ ነው።



*swing* (ስዊን)
ማወዛወዝ/ ዥዋዥዌ
Our father made us a swing near the house.
እቤታችን አጠገብ አባቴ ዥዋዥዌ ሰራልን።



*switch* (ስዊች)
ማብሪያ/ለኤሌክትሪክ/
We have electric switches in every room.
በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ መብራት ማብሪያና ማጥፊያ አለን።

*sword* (ሶ:ድ)
ጎራዴ/ በጣም ትልቅ ቢላዋ የድሮ የጦር መሣሪያ
Soldiers don't use swords today.
በአሁኑ ጊዜ ወታደሮች ጎራዴ አይጠቀሙም።



*T,t* (ቲ:)
ሀያኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*table* (ቴይብል)
ጠረጴዛ/ላዩ ጠፍጣፋ የሆነ አራት
እግር ያለው ለስራ፣ ለመመገቢያ
የሚያገለግል ዕቃ/
I put my book on the table.
መጽሀፌን ጠረጴዛው ላይ
አስቀመጥኩት።



*tadpole* ('ታድፖውል)
እጭ/ትንሽ እንቁራሪት/
There are a thousand tadpoles in the lake.
በሀይቁ ውስጥ አንድ ሺ ያህል
የእንቁራሪት እጮች ይገኛሉ።



*tail* (ቴይል)
ጅራት/ጭራ/የእንስሶች ቀጭን ረዘም
ያለ ከኋላ ያለ አካል
Some monkeys have very long tails.
አንዳንድ ዝንጀሮዎች በጣም ረጅም
ጭራ አላቸው።



*tailor* ('ቴይለ)
ልብስ ሰፊ
My brother is a tailor.
ወንድሜ ልብስ ሰፊ ነው።



*take* (ቴይክ)
1. ከነበረበት ቦታ ማንሳት
Take the pen in your hand and write with it.
እስክርቢቶውን አንሳና ፃፍበት።
2. ከነበረበት ቦታ መውሰድ
My sister has taken my sweet.
እህቴ ከረሜላዬን ወሰደችብኝ።

*talk* (ቶ:ክ)
መናገር/በድምፅ ማውራት/
Stop talking and get on with your work.
ማውራትህን አቁምና ስራህን ስራ።

*tall* (ቶ:ል)
ቁመቱ ረጅም

Fofy is a tall boy
ፎፊ ረጅም ልጅ ነው።

*tank* (ታንክ)
1. ጋን/የፈሳሽ ነገር መያዣ ትልቅ የብረት በርሜል/
The hot water tank is leaking.
የሙቅ ውሃው ጋን እያንጠባጠበ ነው።
2. ታንክ/ለጦርነት የሚያገለግል ከብረት የሚሰራ ተሽከርካሪ
A tank has a big gun on top of it.
ታንክ አናቱ ላይ ትልቅ ጠመንጃ አለው።



*tap* (ታፕ)
1. የቧንቧ ውሃ መክፈቻና መዝጊያ
She turned on the tap to fill the sink with water.
ጎፋውን በውሃ ለመሙላት የቧንቧ መክፈቻውን ከፈተችው።




2. በጣት በር ማንኳኳት ወይም መምታት
He tapped on the door before coming in.
ከመግባቱ በፊት በሩን በጣቱ አንኳኳ።

*tape* (ቴይፕ)
1. ነጭ ፕላስተር/የተቀደደን ነገር ለማጣበቅ የሚያገለግል ባለማጣበቂያ ላስቲክ
The teacher fixed the book with tape.
አስተማሪው መፅሀፉን በፕላስተር አጣበቀ።



2. ሙዚቃ ማዘፈኛ መሳሪያ
Can I borrow your music tape?
የሙዚቃ ማጫወቻህን መዋስ እችላለሁ?



*taste* (ቴይስት)
ጣዕም/የምግብ የመጠጥ መጣፈጥ ወይም መጎምዘዝ ወይም መምረር/
This soup tastes very good.
ይህ ሾርባ ጥሩ ጣዕም አለው።

*taxi* (ታክሲ)
ታክሲ/ገንዘብ እየተቀበሉ ሰው የሚያመላልሱ አውቶሞቢሎች
My mother takes a taxi to work everyday.


እናቴ ሁልጊዜ ስራ ለመሄድ ታክሲ ትይዛለች።





*tea* (ቲ፡)
ሻይ
I like a cup of tea with my breakfast.
ከቁርሴ ጋር አንድ ኩባያ ሻይ መጠጣት እወዳለሁ።

*teach* (ቲ፡ች)
ማስተማር
Will you teach me how to swim?
መዋኘት ታስተምረኛለህ?

*teacher* ('ቲ፡ቸ)
አስተማሪ/መምህር
Our teacher showed us how to do our homework.
አስተማሪያችን የቤት ሥራችንን እንዴት እንደምንሰራ አሳዩን።



*team* (ቲ፡ም)
አንድ ላይ የሚሰሩ ወይም የሚጫወቱ ሰዎች ቡድን
I am playing on the football team.
እግር ኳስ ቡድን ውስጥ እየተጫወትኩ ነው።



***tear*** (ቲየ)
1. እንባ/በምናለቅስበት ጊዜ ከአይናችን የሚፈሰው ጨው ጨው የሚል ፈሳሽ/
The man gave the boy a handkerchief to wipe his tears.
ሰውየው ለልጁ እንባውን እንዲጠርግበት መሀረብ ሰጠው።




2. መቅደድ/ጨርቅን/ወረቀትን
He tore his trousers on the nail.
ሱሪውን ምስማር ቀደደበት።

***telephone*** ('ቴለፎውን)
ስልክ/እሩቅ ቦታ ካለ ሰው ጋር ለመነጋገር የሚያገለግል መሳሪያ
I will telephone my sister in Bahirdar.
ባሕር ዳር ላለችው እህቴ ስልክ እደውላለሁ።




*television* ('ቴሌቪዥን)
ቴሌቪዥን/ሰዎቹ አጠገባችን ሳይኖሩ እንድናያቸው፣ እንድንሰማቸው የሚያደርግ መሳሪያ/
We watched the news on the television.
ዜናውን በቴሌቪዥን ተመለከትን።



*tell* ('ቴል)
ለሰው አንድ ነገር መንገር
Will you please tell me what the man was doing?
እባክህን ሰውየው ምን ሲሰራ እንደነበር ልትነግረኝ ትችላለህ?

*temper* ('ቴምፐ)
ስሜት
I hope my father is in a good temper today.
አባቴ ዛሬ ጥሩ ስሜት ውስጥ እንዳለ ተስፋ አደርጋለሁ።

***temperature*** ('ቴምፕረቸ)
1. ትኩሳት/ስንታመም የሚመጣ ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት/
The doctor told me I have a very high temperature. He gave me some medicine.
ሀኪሙ ከፍተኛ ትኩሳት እንዳለኝ ነገረኝ። መድሀኒትም ሰጠኝ።
2. የአየሩ ሁኔታ/ የሙቀት/የቅዝቃዜ መጠን
What is the temperature today? Oh! it is very cold.
ዛሬ የአየሩ መጠን ስንት ነው? በጣም ይበርዳል።


*ten* (ቴን)
አስር/10/
There are ten oranges left.
አስር ብርቱካኖች ተርፈዋል።

*tennis* ('ቴኒስ)
ኳስን በጠፍጣፋ እንጨት እየመቱ የሚጫወቱት የስፖርት ጨዋታ /ቴኒስ/
Beti wore new white shirt to play tennis.
ቤቲ ቴኒስ ለመጫወት አዲስ ነጭ ሸሚዝ ለበሰች።



*tent* (ቴንት)
ድንኳን/ከጨርቅ ወይም ከሸራ


የሚሰራ ጊዜያዊ ቤት ለሃዘን፣ ለሰርግ የሚተከል/
We are sleeping in a tent tonight.
ዛሬ ማታ በድንኳን ውስጥ እንተኛለን።



*term* (ተ:ም)
ተርም/የአንድ የትምህርት ጊዜ ተጀምሮ ፈተና እስከሚሰጥበት ጊዜ ያለው
We have three terms in our school each year.
በየአመቱ በኛ ትምህርት ቤት ሦስት ተርም አለ።

*test* (ቴስት)
ፈተና/ሙከራ/ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ የሚሰጥ ጥያቄ/
How was your History test?
የታሪክ ሙከራህ እንዴት ነበር?

*textbook* ('ቴክስትቡክ)
የመማሪያ መፅሀፍ
I don't have a textbook for mathematics.
የሒሣብ መማሪያ መፅሃፍ የለኝም።



*than* ('ዘን)
ከ...
I am taller than my sister.
እኔ ከእህቴ ረጅም ነኝ።

*thank* (ታንክ)
ማመስገን
Hirut thanked her uncle for the birthday present.
ሂሩት አጎቷን ለልደቷ ስጦታ ስለሰጣት አመሰገነችው።

*that* (ዛት)
ያ/ያች
That is my pen.
ያ የኔ እስክርቢቶ ነው።

*then* (ዜን)
1. ከዚያ በሁዋላ
First they ate their dinner. Then they had coffee.
መጀመሪያ እራታቸውን በሉ ከዚያ በኋላ ቡና ጠጡ።
2. ያኔ/በዚያን ጊዜ/
They were living in Angola then.
በዚያን ጊዜ አንጎላ ይኖሩ ነበር።

*there* (ዜየ)
እዚያ
I put the three books over there.
ሦስቱንም መፅሀፎች እዚያ አስቀመጥኳቸው።

*these* (ዚ:ዝ)
እነዚህ አጠገባችን ያሉት
These are my sisters' friends.
እነዚህ የእህቶቼ ባልንጀሮች ናቸው።

*thick* (ቲክ)
ወፍራም
The bread is cut in thick slices.
ዳቦው በወፍራም በወፍራሙ ተቆርጧል።




*thief* (ቲ:ፍ)
ሌባ/የሌላውን ሰው ንብረት ሳይታይ የሚወስድ ሰው/
The police caught the thief in our house.
ፖሊሱ ሌባውን ከእኛ ቤት ያዘው።

*thin* (ቲን)
ቀጭን
That boy is very thin. Is he ill?
ያ ልጅ በጣም ቀጭን ነው ታሟል እንዴ?


*thing* (ሲ'ግ)
ስሙ የማይታወቅ ነገር
What is that thing lying on the road?
ያ መንገዱ ላይ የተጋደመው ነገር ምንድነው?

*think* (ቲንክ)
ማሰብ/በአዕምሮ ማሰላሰል
Think hard before you give your answer.
መልስ ከመስጠትህ በፊት በደምብ አስብ።

*third* (ተ:ድ)
1. ሲሶ/ከሶስት ነገሮች አንዱ/ አንድ ሶስተኛ
I want a third of the bread.
የዳቦውን ሲሶ እፈልጋለሁ።



2. ሶስተኛ/ውድድርን ከሁለት ሰዎች በኋላ የጨረሰ/ያሸነፈ



*thirsty* (ተ:ስ·ቲ)
ውሃ የጠማው/በጣም ውሃ መጠጣት የፈለገ/
I am very thirsty after that long walk.
ከረጅሙ ጉዞ በኋላ ውሃ በጣም ጠምቶኛል።

*thirteen* (ተ:·ቲን)
አስራ ሶስት/13
In Ethiopian calendar there are thirteen months in a year.
በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር በአመት ውስጥ አስራ ሶስት ወራት አሉ።

*thirty* (ተ፡ቲ)
ሰላሳ/30/
My father is thrity years old.
አባቴ ሰላሳ አመቱ ነው።

*this* (ዚስ) ተስ-
ይህ/ አጠገብ ያለ ነገር
This is my house .
ይህ የኔ ቤት ነው።

*those* (ዘውዝ)
እነዚያ ራቅ ብለው ያሉት
Those are my classmates.
እነዚያ የክፍል ጓደኞቼ ናቸው።

*thousand* ('ታውዝንድ)
ሺህ/1000/
There were one thousand people at the football match.
በእግር ኳስ ግጥሚያው ቦታ አንድ ሺህ ሰዎች ነበሩ።

*thread* (ትሬድ)
ክር/ልብስ ሲቀደድ ለመስፊያ የሚያገለግል በጣም ቀጭን ገመድ
I sewed on the button with a needle and thread.
ቁልፉን በመርፌና በክር ሰፋሁት።

*three* (ትሪ፡)
ሶስት/3/
I called him three times on the telephone.
ሦስት ጊዜ ስልክ ደወልኩለት።

*throat* (ትረውት)
ጉሮሮ/ከአፍ ወደ ሆዳችን ምግብ የሚያልፍበት የሰውነት አካል
My mother has a sore throat.
እናቴ ጉሮሮዋን አሚታል።



*through* (ስሩ፡)
በአንድ ነገር ውስጥ ማለፍ
We walked through the forest.
በጫካው ውስጥ ሄድን።

*throw* (ስረው)
መወርወር/መጣል
Can you throw that stick across the river?
ያንን እንጨት ወንዙን አሻግረህ ልትወረውረው ትችላለህ?




*T-shirt* (ቲ፡ሸ፡ት)
ቲ- ሸርት/ ሸሚዝ አከል ከነቴራ
I love to wear a T-shirt.
ቲ-ሸርት መልበስ እወዳለሁ።



*thumb* (ተም)
አውራ ጣት
Your thumb helps you to hold things.
አውራ ጣትህ እቃዎችን ለመያዝ ይረዳሀል።




*thunder* (ተንደ)
ነጐድጓድ/በዝናብ ጊዜ ከሰማይ ላይ የሚሰማ ሃይለኛ ድምፅ
I hid under the bed when I heard the thunder.
ነጎድጓድ ስሰማ አልጋ ስር ተደበቅኩ።



*Thursday* (ተ፡ዝዴይ)
ሀሙስ/የሳምንቱ 5ኛ ቀን/
My brother is going fishing on Thursday.
ወንድሜ ሀሙስ እለት አሳ ለማጥመድ ይሄዳል።

*tick* (ቲክ)
1. የሰአት ድምፅ
That ticking clock is keeping me awake.
ቲክ...ቲክ የሚለው የሰአቱ ድምፅ ከእንቅልፌ ቀሰቀሰኝ።
2. ማረም/የፈተና ወይም የክፍል ስራን ምልክት ማድረግ
The teacher ticked my homework.
አስተማሪው የቤት ሥራዬን አረመልኝ።
3. መዥገር/ ሰውነት ላይ ተለጥፎ ደም የሚመጥ/
A tick bit the dog.
ውሻውን መዥገር ነከሰው።

*ticket* ('ቲኪት)
ትኬት/አንድ ነገር ለማድረግ ለምሳሌ ቲያትር/ ወደ ኳስ ሜዳ ለመግባት በገንዘብ የሚገዛ ወረቀት/
I am going to buy a ticket for the match.
ግጥሚያውን ለማየት ትኬት መግዛቴ ነው።



*tickle* ('ቲክል)
መኮርኮር/ሰውነትን በተለይ ብብትን፣ የእግርን ስር በመንካት ማሳቅ/

Please don't tickle my feet.
እባክህ እግሬን አትኮርኩረኝ።

*tide* (ታይድ)
ማዕበል/ውሀውን ወዲያ ወዲህ የሚያወዛውዝ ሃይለኛ የባህር ንፋስ
The tide comes in twice a day.
ማዕበሉ በቀን ሁለቴ ይነሣል።

*tidy* ('ታይ.ዲ)
ንፁህ/ምንም ቆሻሻ የሌለበት/የፀዳ
I have a tidy kitchen.
ንፁህ ማዓድቤት አለኝ።

*tie* (ታይ)
1.ከረባት/ከሸሚዝ በላይ አንገት ላይ የሚታሰር ቀጭን ጨርቅ
Men wear ties under the collar of their shirts.
ወንዶች ከሸሚዛቸው ኮሌታ ስር ከረባት ያስራሉ።



2. በገመድ ወይም በሰንሰለት ማሰር
The flowers are tied together.
አበቦቹ አንድ ላይ ታስረዋል።



*tiger* ('ታይገ)
ነብር/ቁጡ ዥንጉርጉር የዱር አውሬ/
The tiger belongs to the cat family.
ነብር የድመት ዝርያ ነው።



*till* (ቲል)
1. /እስከ/አንድ ነገር እስኪሆን ድረስ
Can you wait till my mother comes?
እናቴ እስክትመጣ ልትቆይ ትችላለህ?
2. ገንዘብ ማስቀመጫ ሳጥን
Always lock the till when you leave the shop.
ሁልጊዜ ከሱቁ ስትወጣ የገንዘብ ሳጥኑን ቆልፈው።

*time* (ታይም)
1. አንድ ነገር የሚሆንበት ጊዜ
This is going to take a long time.
ይህ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ነው።
2. ሰአት
It is time to go to bed.
አሁን የመተኛ ሰዓት ነው።



*tin* (ቲን)
ጣሳ/ውስጡ ምግብ ወይም ሌላ ነገር የሚታሸግበት ክብ ስሩና ላዩ ድፍን ቆርቆሮ
I ate a tin of beans.
አንድ ጣሳ ባቄላ በላሁ።



*tip* (ቲፕ)
1. ጫፍ/ የአንድ ነገር የላይኛው የመጨረሻው ክፍል/
The tip of this pencil is broken.
የእርሳሱ ጫፍ ተሰብሯል።
2. አንድን ነገር መጣል በተለይ ቆሻሻን
He tipped the rubbish over the floor.
ቆሻሻውን ወለሉ ላይ ጣለው።

*tired* (ታይየድ)
መድከም/መሰልቸት
The little boy is very tired.
ትንሹ ልጅ በጣም ደክሞታል።

*to*(ቶ)
ወደ
I go to school everyday.
በየቀኑ ወደ ትምሕርት ቤት እሔዳለሁ።

*toad* (ተውድ)
ጉርጥ/እንቁራሪት የሚመስል አይነ ትልልቅ እንስሳ/ ጓጉንቸር
Toads have rough, dry skins.
ጓጉንቸሮች ሸካራና ደረቅ ቆዳ አላቸው።



*toast* (ተውስት)
የተጠበሰ ዳቦ/የተቆራረጠ
My father made toast for breakfast.
አባቴ ለቁርስ የዳቦ ጥብስ አዘጋጀ።

*today* (ተ'ዴይ)
ዛሬ/ይሄ ያለንበት ቀን
Today we are not going to school.
ዛሬ ትምህርት ቤት አንሄድም።

*toe* (ተው)
የእግር ጣቶች
You have five toes on each foot.
በእያንዳንዱ እግርህ ላይ አምስት ጣቶች አሉህ።



***toffee*** ('ቶፊ)
ከወተት የሚሰራ ከረሜላ
I bought a bag of toffees in the shop.
ከሱቅ አንድ ከረጢት ከረሜላ ገዛሁ።

***together*** (ቱ'ጌዘ)
ባንድነት/ከአንድ በላይ ሰዎች ወይም ነገሮች አንድ ላይ አብረው/
The three children carried the sticks together.
ሶስቱ ልጆች እንጨቶቹን አብረው ተሸከሙ።



***toilet*** ('ቶይለት)
መፀዳጃ ቤት
We have a toilet in our house.
እቤታችን መፀዳጃ ቤት አለን።

***tomato*** (ተ'ማ:ተው)
ቲማቲም/ሲበስል ቀይ የሚሆን ውስጡ ጥቃቅን ፍሬዎች ያሉት አትክልት
You can eat raw tomatoes in salad.
በሰላጣ ጥሬ ቲማቲም መብላት ትችላለህ።



***tomorrow*** (ተሞረው)
ነገ/ከዛሬ ቀጥሎ ያለው ቀን
I'm going to school tomorrow.
ነገ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

***tongue*** (ተን)
ምላስ/አፋችን ውስጥ የሚገኝ ስንናገር፣ ስንበላ የሚንቀሳቀስ አካል
You taste with your tongue.
በምላስህ ትቀምሳለህ።



***too*** (ቱ:)
1. ደግሞ/ካሉት በተጨማሪ/
Can I come too?
እኔም ልመጣ እችላለሁ?
2. እጅግ በጣም ብዙ
You have given me too much rice.
እጅግ በጣም ብዙ ሩዝ ሰጥተኸኛል።

***tool*** (ቱ:ል)
የስራ መሳሪያ/ስራ ለመስራት የሚያገለግል
My brother keeps his tools in the tool shed.
ወንድሜ የእጅ መሳሪያውን በሳጥን ውስጥ ያስቀምጣል።



*tooth* (ቱ:ስ)
ጥርስ/አፋችን ውስጥ ያለ ለምግብ መብያ የሚያገለግለን ጠንካራ አጥንት/
You use your teeth to bite and chew food.
ለመንከስና ምግብ ለማኘክ ጥርሶችህን ትጠቀማለህ።



*toothbrush* (ቱ:ስ ብረሽ)
የጥርስ ማጠቢያ ብሩሽ
Do not let anybody to use your toothbrush.
የጥርስ ብሩሽህን ማንም እንዲጠቀምበት አትፍቀድ።

*toothpaste* ('ቱ:ስፔይስት)
የጥርስ ማጠቢያ ሳሙና
Put plenty of toothpaste on your brush to clean your teeth.
ጥርስህን ለማፅዳት በርከት ያለ የጥርስ ሳሙና ብሩሽህ ላይ አድርግ።



*top* (ቶፕ)
አናት/ጫፍ/የአንድ ነገር የመጨረሻው የላይኛው ክፍል/
The man climbed to the top of the ladder.
ሰውየው ወደ መሰላሉ አናት ወጣ።



*torch* (ቶ:ች)
1. ባትሪ/በእጅ የሚያዝ ብርሃን የሚሰ
You need batteries to make a torch work.
የእጅ ባትሪውን ለማሰራት ባትሪ ያስፈልግሃል።



2. ችቦ
My father lit the torch.
አባቴ ችቦውን ለኮሰው።



*touch* (ተች)
ነካ/አንድን ነገር በእጁ ዳሰሰ/
Do not touch that fire, you will burn your hand.
ያንን እሳት እንዳትነካ እጅህን ያቃጥልሀል።

*towards* (ተዎ፡ድዝ)
ወደ አንድ ቦታ /ነገር/ መሄድ
The baby giraffe ran towards its mother.
ግልገሏ ቀጭኔ ወደ እናቷ ሮጠች።

*towel* ('ታውል)
/ፎጣ/የፊት የገላ ማድረቂያ ጨርቅ
The man dried himself with a towel.
ሰውየው ሰውነቱን በፎጣ አደረቀው።


*town* (ታውን)
ከተማ/ቤቶች በጣም ተቀራርበው የሚገኙበት አካባቢ.
There is a large hospital in our town.
በከተማችን ትልቅ ሆስፒታል አለ።

*toy* (ቶይ)
አሻንጉሊት/ከጨርቅ/ከፕላስቲክ የሚሰሩ የልጆች መጫወቻዎች
Can I play with your toys?
በአሻንጉሊቶችህ ልጫወት እችላለሁ?

*track* (ትራክ)
እግረኛ ብቻ የሚያስኬድ መንገድ
We followed the track down to the river.
ወደ ወንዙ የሚወስደውን የእግር መንገድ ተከተልን።

*traffic* ('ትራፊክ)
በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ነገር ለምሳሌ ሰው፣ መኪና
There is a lot of traffic on the road today.
ዛሬ በመንገዱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የመኪና መጨናነቅ አለ።

*train* (ትሬይን)
1. ባቡር/በሃዲድ ላይ ብዙ ፉርጎዎች እየጎተተ የሚሄድ ተሽከርካሪ
The train was bringing coal from the mine.
ባቡሩ ከማዕድን ጉድጓድ ውስጥ ከሰል ሲያመጣ ነበር።



2. አንድ ስራ እንዲሰሩ ለማድረግ የሚሰጥ ስልጠና
He trained the horses to jump fences.
ፈረሶቹን አጥር መዝለል አሰለጠናቸው።

*transport* ('ትራንስፖ፡ት)
መጓጓዣ/ ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ የምንገለገልበት ማንኛውም ነገር
Cars, airplanes, ships, trains, are all means of transport.
መኪናዎች፣ አይሮፕላኖች፣ መርከቦች፣ ባቡሮች፣ ሁሉም የመጓጓዣ ዓይነቶች ናቸው።

***trap*** (ትራፕ)
ወጥመድ/አንድ አውሬን ለመያዝ የሚዘጋጅ መሳሪያ
The leopard is caught in the trap.
አቦሸማኔው በወጥመዱ ተያዘ።

***travel*** (ትራቭል)
መሄድ/መጓዝ/ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደሌላ ቦታ
My father has travelled all over the world.
አባቴ በአለም በሙሉ ተጉዟል።

***tray*** (ትሬይ)
ትሪ/ዝርግ ሳህን
I will carry the tray of dishes to the table.
በዝርግ ሳህን ያለውን ምግብ ወደ ጠረጴዛው እወስደዋለሁ።



***treasure*** (ትሬገር)
ንብረት/ዋጋ ያላቸው እቃዎች
The boys found the treasure buried in the woods.
ልጆቹ በጫካ ውስጥ የተቀበረ ንብረት አገኙ።

***treat*** (ትሪ፡ት)
መንከባከብ/ አንድን ነገር በጥሩ ሁኔታ መያዝ
That man treats his dog very badly: He beats it all the time.
ያ ሰው ውሻውን በጥሩ ሁኔታ አይንከባከበውም ሁልጊዜ ይመታዋል።

***tree*** (ትሪ፡)
ዛፍ/ቅጠልና ግንድ ያለውረጅም ተክል
The elephants rested under the tree.
ዝሆኖቹ በዛፉ ስር እረፍት አደረጉ።



***triangle*** ('ትራይአንግል)
ባለ ሶስት ማእዘን ቅርጽ
Draw a triangle in your book.
ደብተርህ ላይ ሦስት ማእዘን ሳል።



***trick*** (ትሪክ)
ሰውን ማታለል/ማሞኘት
He tricked me into giving him the money.
ገንዘቡን እንድሰጠው አታለለኝ።

***trip*** (ትሪፕ)
መደናቀፍ/በመራመድ ላይ እያሉ እግርን በአንድ ነገር መመታት/

The girl tripped over the stone and fell on her knees.
ልጅቷ ድንጋዩ አደናቅፏት በጉልበቷ ወደቀች።

*trot* (ትሮት)
ደንግላሳ/ቀስ ብሎ መጋለብ ለፈረስ
The horse trotted over to the man.
ፈረሱ ወደ ሰውየው ደንግላሳ ጋለበ።

*trouble* (ትረብል)
ችግር/የሚያስጨንቅ ወይም የሚያናድድ/
He is in trouble but I can not help him.
ችግር ውስጥ ነው ግን ልረዳው አልችልም።

*trousers* (ትራው)
ሱሪ/ከወገብ በታች ያለን ሰውነት የሚሸፍን እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ ልብስ
My brother is wearing his brown trousers today.
ወንድሜ ዛሬ ቡና አይነት ሱሪ ለብሷል።



*truck* (ትረክ)
1. ፉርጎ/በባቡር የሚጎተት ጋሪ
The train pulled trucks full of fruits.
ባቡሩ በፍራፍሬ የተሞሉ ጋሪዎችን ጐተተ።
2. የጭነት መኪና/ትልልቅ እቃዎችን የሚጭን መኪና
The truck has a lot of noise.
የጭነት መኪናው ከፍተኛ ድምፅ አለው።




*true* (ትሩ)
እውነት የሆነ/ትክክል የሆነ
It is true that you are a human being.
ሰው መሆንህ እውነት ነው።

*trunk* (ትረንክ)
1. የዛፍ ዋና አካል ግንዱ
We will cut the tree trunk up for firewood.
የዛፉን ግንድ ለእሳት ማንደጃነት እንቆርጠዋለን።
2. የልብስ/ትልቅ ሳጥን
Mom packed our old clothes in the trunk.
እማዬ አሮጌ ልብሶቻችንን ትልቁ ሳጥን ውስጥ ከተተችው።



3. ኩምቢ/የዝሆን አፍንጫ/
Only elephants have trunk.
ዝሆኖች ብቻ ናቸው ክምቢ ያላቸው።



*truth* (ትሩስ)
እውነት
You didn't tell me the truth about your father.
ስለአባትህ እውነቱን አልነገርከኝም።

*try* (ትራይ)
አንድን ነገር ለማድረግ መሞከር
I tried to fix the toy.
አሻንጉሊቱን ለመጠገን ሞከርኩ።

*tube* (ትዩ፡ብ)
ቱቦ/ ቀጭን ረጅም መሃሉ ቀዳዳ ያለው ፈሳሽ እና የመሳሰሉትን ነገር መያዣ/ማመላለሻ
Toothpastes are sold in tubes.
የጥርስ ሣሙናዎች በቱቦ ይሸጣሉ።



*Tuesday* ('ትዩ፡ዝዴይ)
ማክሰኞ/የሳምንቱ ሶስተኛው ቀን
My sister is going to Addis Ababa on Tuesday.
እህቴ ማክሰኞ ወደ አዲስ አበባ ትሄዳለች።


*tug* (ተግ)
መመንጨቅ/አንድን ነገር ለመንቀል በሃይል መጎተት
He tugged at the weed, but he could not move it.
አረሙን በሃይል ጎተተው ግን ሊነቅለው አልቻለም።

*tunnel* ('ተንል)
ዋሻ/በመሬት ውስጥ ለውስጥ የተቆፈረ መንገድ/
The tunnel was five kilometres long.
ዋሻው አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት አለው።



*turn* (ተ፡ን)
መዞር/መሽከርከር
Push the pedals and the wheels will turn round.
ፔዳሉን ስትገፋው ጎማዎቹ ይሽከረከራሉ።

*tusk* ('ተስክ)
የዝሆን ጥርስ
The elephant has a broken tusk.
ዝሆኑ የተሰበረ ጥርስ አለው።



*twelve* (ትዌልቭ)
አስራ ሁለት/12/
There are twelve months in a year in the gregorian calendar
በጎርጎርሣውያን አቆጣጠር አስራ ሁለት ወራት አሉ።

*twenty* (ትዌንቲ)
ሀያ/20/
I have twenty books in the house.
ቤቴ ሀያ መጽሀፎች አሉኝ።

*twice* (ትዋይስ)
ሁለት ጊዜ
That is a good book. I read it twice.
ያ ጥሩ መጽሃፍ ነው ሁለት ጊዜ አንብቤዋለሁ።

*twig* (ትዊግ)
ቀጫጭን የዛፍ ቅርንጫፎች አርጩሜ ወይም ጭራሮ
You can use the twigs to light the fire.
እሳቱን ለማንደድ ጭራሮዎቹን መጠቀም ትችላለህ።

*twin* (ትዊን)
መንታ/እኩል ከአንድ እናት በአንድ ጊዜ ከተወለዱ ልጆች አንዱ/አንዷ
One twin is a boy. The other twin is a girl.
አንዱ መንትያ ወንድ ነው። ሌላዋ መንትያ ሴት ናት።



*two* (ቱ)
ሁለት/2/
A bicycle has two wheels.
ብስክሌት ሁለት ጎማዎች አሉት።

*type* (ታይፕ)
1. አይነት
What is your blood type?
የደምህ አይነት ምንድን ነው?
2. መፃፍ/ታይፕ ማድረግ በዕህፈት መኪና ወይም በኮምፒውተር
She types all her letters on her computer.
ሁሉንም ደብዳቤዎቿን በኮምዩተሩ ትፅፋለች።



*tyre* (ታይየ)
ጎማ/መኪናዎችና ሌሎች ተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠም ክብ ቱቦ
My bicycle has a tire.
ብስክሌቴ ጎማ አለው።



# Uu

*U, u* (ዩ፡)
21ኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*ugly* ('ኧግሊ)
የማያምር/አስቀያሚ
That is a strange animal. It looks very ugly.
ያ ለየት ያለ እንስሣ ነው። በጣም አስቀያሚ ይመስላል።

*umbrella* (ኧም'ብሬለ)
ዣንጥላ/ለዝናብ ለፀሀይ መከላከያ የሚዘረጋ ላዩ ክብ ሆኖ መሃሉ ዘንግ ያለው ጨርቅ
It is raining. Put up your umbrella.
ዝናቡ እየዘነበ ነው። ዣንጥላህን ዘርጋ።



*unable* (ኧን'ኤይብል)
ሊሰራ ሊደረግ የማይቻል ነገር
He broke his leg. He is unable to walk.
እግሩ ተሰበረ። ለመራመድ አይችልም።

*uncle* ('ኧንክል)
አጎት/የአባት ወይም የእናት ወንድም/
I have only one uncle.
አንድ አጎት ብቻ አለኝ።

*under* ('ኧንደ)
ከአንድ ነገር ስር
My mother is sitting under the tree.
እናቴ ከዛፉ ስር ተቀምጣለች።



*understand* (ኧንደ'ስታንድ)
አንድን ነገር መረዳት
I understand the words in that book.
በመጽሃፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት ተረዳሁ።

*undo* (ኧን':ዱ)
የታሰረውን መፍታትና መክፈት
Undo the string!
ገመዱን ፍታ!

*unhappy* (ኧን'ሀፒ)
ማዘን፣አለመደሰት፣ መከፋት
She is very unhappy because of her lost puppy.
በጠፋችው ቡችላዋ ምክንያት በጣም አዝናለች።

*uniform* ('ዩ:ኒፎ:ም)
የትምህርት ቤት ወይም የስራ መለያ ልብስ/ መለዮ
I always wear my school uniform.
ሁልጊዜ የትምህርት ቤቴን መለያ ልብስ እለብሣለሁ።

*untidy* (አን'ታይዲ)
ንፁህ ያልሆነ/ ቆሻሻ
Take a shower you are very untidy!
በጣም ስለቆሸሽክ ገላህን ታጠብ!


*untie* (አን'ታይ)
የታሰረን ነገር መፍታት
He untied his laces and took his shoes off.
የጫማ ክሮቹን ፈቶ ጫማዎቹን አወለቀ።

*until* (አን'ቲል)
እስከ...
Every night I work until nine o'clock.
ሁልጊዜ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት እሠራለሁ።

*up* (አፕ)
ወደላይ
Don't try to go up; it is dangerous.
ወደላይ ለመሄድ አትሞክር አደገኛ ነው።

*upset* (አፕ'ሴት)
ማዘን፣መናደድ፣ መቆጣት
My mother is upset. She broke a dish.
እናቴ ሳህን ስለሠበረች ተናደደች።

*upside-down* (አፕሳይድ'ዳውን)
የላዩን ወደ ታች መሆን/መገልበጥ/
The bus is upside-down because of the accident.
አውቶብሱ በአደጋው ምክንያት ተገልብጧል።



*use* (ዩ:ስ)
አንድን ነገር መጠቀም
I used soap and water to wash my car.
መኪናዬን ለማጠብ ሳሙናና ውሃ ተጠቀምኩ።

*useful* ('ዩ:ስፍል)
ጠቃሚ
Watch is very useful.
ሰአት በጣም ጠቃሚ ነው።

*usual* ('ዩ:ዡወል)
ሁልጊዜ ተደጋግሞ የሚደረግ ነገር/ የተለመደ
I am going to school at the usual time today.
ዛሬም በተለመደው ሰአት ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

# Vv

*V, v* (ቪ:)
22ኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*valley* (ቫሊ)
ሸለቆ/በከፍተኛ ቦታዎች መሃል ያለ ዝቅተኛ ቦታ
There is a little valley with a river in the hills.
ከኮረብታዎቹ መሃል ትንሽ ሸለቆና ወንዝ አለ።



*valuable* (ቫልዩወብል)
ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነገር
That is a big car. It must be very valuable.
ያ ትልቅ መኪና ነው። ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሳይሆን አይቀርም።

*van* (ቫን)
ከቤት መኪና ከፍ ከአውቶብስ አነስ ያለ መኪና
They took us to Awasa by their red van.
በቀዩ መኪናቸው ወደ አዋሣ ወሰዱን።



*vanish* (ቫኒሽ)
መጥፋት/መሰወር
Can you make the cake vanish? Yes, I can eat it.
ኬኩ እንዲሰወር ማድረግ ትችላለህ? አዎ፣ እበላዋለሁ።

*vase* (ቫ:ዝ)
የአበባ ማስቀመጫ ብርጭቆ ወይም ገንቦ
Put the flowers in that beautiful vase.
አበቦቹን በዚያ ቆንጆ የአበባ ማስቀመጫ ውስጥ አስቀምጣቸው።



*vegetable* (ቬጀተብል)
የሚበሉ ተክሎች
Cabbages and carrots are vegetables.
ጎመንና ካሮት የሚበሉ ተክሎች ናቸው።

*vehicle* (ቪ:የክል)
/ተሽከርካሪ/ ሰዎች የሚጓጓዙባቸው ነገሮች በሙሉ ብስክሌት፣ ባቡር፣ መኪና የመሣሰሉት
Which vehicle is taking us to town?
ወደ ከተማ የሚወስደን የትኛው ተሽከርካሪ ነው?

*vein* (ቬይን)
**የደም ስር በሰውነት ውስጥ ደምን የሚያዘዋውር ቀጭን ቱቦ**
Look! You can see veins in his hand.
**ተመልከት የእጁን የደም ስሮች ማየት ይቻላል።**

*verb* (ቨ፡ብ)
**ግስ/ድርጊትን የሚገልጽ ቃል/**
The boy hit the goat. 'Hit' is a verb.
**ልጁ ፍየሏን *መታ*። '*መታ*' የሚለው ቃል ድርጊትን የሚገልፅ ግስ ነው።**

*verse* (ቨ፡ስ)
**ስንኝ/የግጥም የመጀመሪያ ሁለት መስመሮች/**
I will sing the first verse. You can sing the second verse.
**እኔ የመጀመሪያውን ስንኝ እዘፍናለሁ አንተ ሁለተኛውን ስንኝ መዝፈን ትችላለህ።**

*very* (ቬሪ)
**በጣም**
Icecream is very cold.
**አይስክሬም በጣም ቀዝቃዛ ነው።**

*vest* (ቬስት)
**ካኔቴራ**
It is very cold. He is wearing a vest and a jersey.
**በጣም ስለሚበርድ ካኔቴራ እና ሹራብ ለብሷል።**



*view* (ቫዩ)
**እይታ/አንድ ቦታ ሆኖ ማየት የሚቻለው ነገር ሁሉ**
There is a good view of the town from our house.
**ከቤታችን ሆኖ ከተማው በደንብ ይታያል።**

*village* (ቪሊጅ)
**ሰፈር/ መንደር**
We live in a village near the river.
**ከወንዙ አጠገብ ያለች መንደር ውስጥ እንኖራለን።**



*vinegar* (ቪነገ)
**ኮምጣጤ/ የሠላጣ ቲማቲም መስሪያ ጉምዛዛ ፈሳሽ**
I eat vinegar with fish and chips.
**ከአሳ እና ከድንች ጥብስ ጋር ኮምጣጤ እበላለሁ።**

*violin* (ቫይዮሊን)
**እንደማሲንቆ ያለ የክር የሙዚቃ መሣሪያ**

I can play the violin.
ቫዮሊን መጫወት እችላለሁ ::



*visit* ('ቪዚት)
አንድን ሰው ወይም ቦታ ሄዶ ማየት/ መጎብኘት
We visit my father in the hospital everyday.
አባቴን በየቀኑ ሆስፒታል እንጎበኘዋለን።

*voice* ('ቮይስ)
ሲናገሩ ወይም ሲጮሁ የሚሰማ ድምፅ
Keep your voice down. Dad is sleeping.
አባባ ስለተኛ ድምፅህን ዝቅ አድርግ።

*volcano* ('ቮልኬይነው)
እሳተ ጎመራ/ከተራራ የሚወጣ የቀለጠ ድንጋይ/
Look at the fire coming from the volcano!
ከእሳተ ጎመራው የሚወጣውን እሳት ተመልከት!



*vowel* ('ቫወል)
አናባቢ/በእንግሊዝኛ ውስጥ a e i o u በአማርኛ አ ኡ ኢ ኣ ኤ እ ኦ ፊደላት አናባቢ ፊደላት ይባላሉ
How many vowels are there in the English alphabet?
በእንግሊዝኛ ፊደል ውስጥ ስንት አናባቢ ፊደላት አሉ?

*vulture* ('ቨልቸ)
ጆፌ አሞራ/ ትልቅ የሞቱ እንስሳትን የሚበላ አሞራ
Look at the vultures. They must see a dead animal.
ጆፌ አሞራዎቹን ተመልከት የሞተ እንስሣ ሣያዩ አይቀሩም።



# Ww

*W,w* ('ደብልዩ:)
ሀያሶስተኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*wade* (ዌይድ)
በውሃ ውስጥ መሄድ
The swimmer can made easily.
ዋናተኛው ውሃ ውስጥ በቀላሉ መሄድ ይችላል።

*wag* (ዎግ)
መወዛወዝ/ከአንዱ ጎን ወደ ሌላው ጎን
The dog is happy. It is wagging its tail.
ውሻው ደስ ብሎታል ጭራውን እያወዛወዘ ነው።

*wagon* ('ዋገን)
ጋሪ/በፈረስ ወይም በበሬ የሚጎተት
The wagon is carrying four people.
ጋሪው አራት ሰዎችን አሳፍሯል።

*waist* (ዌይስት)
ወገብ/ከሆድና ከቂጥ መሃከል ያለው የሰውነት አካል
She is wearing a belt round her waist.
ወገቧ ላይ ቀበቶ ታጥቃለች።

*wait* (ዌይት).
መጠበቅ
Mulu is waiting for the bus.
ሙሉ አውቶብስ እየጠበቀች ነው።

*wake* (ዌይክ)
አለመተኛት /መንቃት
I wake up when the sun rises.
ፀሃይ ስትወጣ እነቃለሁ።

*walk* (ዎ:ክ)
በእግር መራመድ
I walk to school every morning.
በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ወደ ትምሕርት ቤት በእግሬ እሄዳለሁ።



*wall* (ዎ:ል)
1. የቤት ግድግዳ
We can put the pictures on the wall.
ስዕሎቹን ግድግዳው ላይ መስቀል እንችላለን።
2. የግንብ አጥር
We will build a wall to keep the cows in.
ላሞቹን ለመጠበቅ የግንብ አጥር እናጥራለን።



*walrus* (ዋ:ልረስ)
የባህር እንስሳ/ ዋለሩስ/
Walrus loves to play in the ice.
ዋለሩስ በበረዶ መጫወት ይወዳል።



*want* (ዎንት)
አንድ ነገር መፈለግ
I want some bread and butter.
ጥቂት ዳቦና ቅቤ እፈልጋለሁ።

*war* (ዎ:)
ጦርነት/በአገሮች መካከል የሚደረግ ውጊያ
Many soliders died in the war.
ብዙ ወታደሮች በጦርነቱ ሞቱ።



*warm* (ዎ:ም)
በጣም ያልሞቀ/ለብ ያለ/
The fire warmed the room.
እሳቱ ቤቱን ሞቅ አደረገው።




*was* (ዎዝ)
የመሆን ግስ ያለፈ ጊዜን የሚያመለክት
I was in school until six o'clock.
እስከ ስድስት ሰአት ትምህርት ቤት በርኩ።

*wash* (ዎሽ)
አንድን ነገር በውሃ ማጠብ
My mother washed my clothes.
እናቴ ልብሶቼን አጠበቻቸው።

*wasp* (ዎስፕ)
ተርብ/ተናዳፊ ትልቅ ዝንብ/
A wasp is a dangerous insect.
ተርብ አደገኛ ነፍሳት ነው።



*watch* (ዎች)
1. እጅ ላይ የሚታሰር ሰዓት
Have you got a watch? What time is it?
ሰአት አለህ? ስንት ሰአት ነው?



2. መመልከት
Watch the snail, it moves very slowly.
ቀንድ አውጣውን ተመልከት በጣም በቀስታ እየተንቀሳቀሰ ነው።

*water* (ዎ:ተ)
ውሀ
It is healthy to drink six cup of water everyday.
በየቀኑ ስድስት ብርጭቆ ውሃ መጠጣት ጤንነት ነው።



*wave* (ዌይቭ)
እጅን ማወዛወዝ ለሠላምታ
There is your aunt. Wave your hand.
አክስትህ ያቻትና እጅህን አወዛውዝላት።

*wax* (ዋክስ)
ሰም/ሻማ የሚሠራበት
Wax is a part of honey.
ሰም የማር አካል ነው።

*way* (ዌይ)
1. መንገድ መሄጃ
Take that road. That's the way to the village.
ያንን መንገድ ተከተል ወደ መንደሩ የሚያስገባህ እሱ ነው።
2. አንድ ነገር የመስራት መንገድ/ አቅጣጫ
Kick the ball this way.
ኳሷን በዚህ አቅጣጫ ምታት።

*weak* (ዊ:ክ)
ደካማ/ ጠንካራ ያልሆነ
The old man is too weak to walk.
ሽማግሌው ለመራመድ እንኳን በጣም ደካማ ናቸው።



*wear* (ዌየ)
ልብስ መልበስ
I am wearing a green dress today.
ዛሬ አረንጓዴ ልብስ ለብሻለሁ።

*weather* (ዌዘ)
የአንድ ቀን የአየር ሁኔታ
It is a sunny weather today.
ዛሬ የአየሩ ሁኔታ ፀሃያማ ነው።
*web* (ዌብ)
የሸረሪት ድር

The spider trapped the fly by her web.
ሸረሪቷ ዝንቧን በድሯ አጠመደቻት።

*wedding* (ዌዲንግ)
ሰርግ/የወንድና ሴት ሙሽሮች የሚጋቡበት ጊዜ/
I went to my sister's wedding.
ወደ እህቴ ሰርግ ሄድኩ።



*Wednesday* (ዌንዝዴይ)
/ረቡዕ/ የሳምንቱ 4ኛ ቀን
We always do sport on Wednesday.
ሁልጊዜ ረቡዕ ረቡዕ ስፖርት እንሠራለን።

*weed* (ዊ:ድ)
አረም/ ከተክሎች ጋር ሳይዘሩ የሚበቅል የማይፈለግ ተክል
There are more weeds than flowers in the garden.
በአትክልት ቦታው ውስጥ ከአበቦቹ አረሞቹ ይበዛሉ።



*week* (ዊ:ክ)
ሳምንት/ሰባት ቀናት/በአንድነት የሚጠሩበት ከእሁድ እስከ ቅዳሜ
My father works five days a week.
አባቴ በሳምንት አምስት ቀን ይሠራል።

*weigh* (ዌይ)
የአንድ ነገር ክብደት
My father is a big man he weighs 92 Kg.
አባቴ ግዙፍ ሰው ነው። ክብደቱ 92 ኪሎ ነው።


*welcome* (ዌልከም)
እንኳን ደህና መጣህ በማለት በደስታ መቀበል
My friend's mother welcomed me to her house.
የጓደኛዬ እናት እቤታቸው በደስታ ተቀበሉኝ።

*well* (ዌል)
1. ጤነኛ መሆን/አለመታመም/
I was ill, but I am well now.
ታምሜ ነበር አሁን ግን ጤነኛ ነኝ።
2. መሬት ላይ የተቆፈረ ጉድጓድ
We get lots of water from the well.
ከጉድጓዱ ብዙ ውሃ እናገኛለን።

*were* (ወ:)
እንደ"was" ሃላፊ ጊዜን የሚገልጽ ሲሆን ይሄ ግን ለብዙ ወይም ከሁለት በላይ ለሆኑ ነገሮች ነው።
I was happy but they were very unhappy.

እኔ ደስተኛ ነበርኩ እነሱ ግን በጣም አልተደሰቱም።

*west* (ዌስት)
ምዕራብ/ፀሀይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ
Our village is to the west of the city.
ሰፈራችን ከከተማው በስተምዕራብ ነው።




*wet* (ዌት)
እርጥብ/ በውሃ የበሰበሰ
It is raining so I am very wet.
ዝናቡ እየዘነበ በመሆኑ አበሰበሰኝ።

*whale* (ዌይል)
አሣነባሪ/በጣም ትልቅ የባህር እንስሣ/
Whales are the biggest animals in the world.
አሣነባሪዎች ከአለም ትልልቆቹ እንስሣት ናቸው።



*what* (ዎት)
ጥያቄ መጠየቅ/ምን?/
What are you doing?
ምን እያደረግህ ነው?

*wheat* (ዊ:ት)
ስንዴ
We can make bread from wheat flour.
ከስንዴ ዱቄት ዳቦ እንጋግራለን።



*wheel* (ዊ:ል)
ጎማ/ መንኩራኩር
1. Bicycles have two wheels. Cars have four.
ብስክሌቶች ሁለት ጎማ አላቸው መኪናዎች ደግሞ እራት ጎማ አላቸው።



2. የመኪና/ የተሽርካሪ መሪ
Wheel is the most important part of a car
መሪ የመኪና በጣም አስፈላጊው አካል ነው።



*when* (ዌን)
መቼ/በየትኛው ጊዜ?
When do you go to school?
መቼ ነው ትምህርት ቤት የምትሄደው?

*where* (ዌየ)
የት ቦታ?
Where are you going?
የት ነው የምትሄደው?

*which* (ዊች)
የትኛውን? ብሎ መጠየቅ
Which dress do you want?
የትኛውን ቀሚስ ትፈልጊያለሽ?

*while* (ዋይል)
በተመሣሣይ ሰአት/ በዛው ጊዜ
While you work, I will read my book.
አንተ በምትሠራበት ጊዜ እኔ መጽሐፌን አነባለሁ።

*whisper* ('ዊስፐ)
ማንሾካሾክ/ ድምፅን በጣም አሣንሶ መናገር/
Don't tell mother. Whisper to me.
ለእናቴ እንዳትነግራት። ለኔ በሹክሹክታ ንገረኝ።

*whistle* ('ዊስል)
1. ማፏጨት
Can you whistle a song for me?
መዝሙር በፉጨት ልትዘምርልኝ ትችላለህ?
2. ፊሽካ
I have a whistle for the soccer referee to blow.
የእግር ኳስ ዳኛ የሚነፋው ፊሽካ አለኝ።



*white* (ዋይት)
ነጭ /የወተት ቀለም/
Swans are white birds.
የውሃ ዶሮዎች ነጫጭ ወፎች ናቸው።


*who* (ሁ:)
ማን?/ስለአንድ ሰው ማንነት መጠየቅ።
Who is that man?
ያ ሰው ማነው?

*whole* ('ሆውል)
የአንድ ነገር በሙሉ
I ate the whole cake.
ኬኩን በሙሉ በላሁ።

*whose* (ሁ:ዝ)
የማን
Whose car is that?
ያ መኪና የማን ነው?

*why* (ዋይ)
ለምን?/የአንድን ነገር ምክንያት ለማወቅ መጠየቅ/
Why did you take my book?
መጽሃፌን ለምን ወሰድክ?

*wide* (ዋይድ)
ስፋት/ከአንዱ ጫፍ እስከ ሌላው ያለው ርቀት/
This is a very wide cloth.
ይህ በጣም ሰፊ ጨርቅ ነው።



*wife* (ዋይፍ)
ሚስት/ባል ያገባች ሴት/
Abebe and his wife have two children.
አበበና ሚስቱ ሁለት ልጆች አሏቸው።


*wild* (ዋይልድ)
ዱር ሜዳ/ጫካ ውስጥ የሚኖር
The forest is full of wild animals.
ጫካው በዱር አራዊት የተሞላ ነው።

*willing* ('ዊሊን)
አንድ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን
He is always willing to help his mother.
እናቱን ለመርዳት ምንጊዜም ፈቃደኛ ነው።


*win* (ዊን)
ማሸነፍ/ በውድድር መቅደም
He won the race.
ውድድሩን አሸነፈ።

*wind* (ዊንድ)
ንፋስ
The wind was very strong.
ንፋሱ በጣም ሃይለኛ ነበር።

*window* ('ዊንዶው)
መስኮት/በግድግዳ መሃል የተከፈተ ቀዳዳ/
Look at through the window. You can see the rain.
በመስኮት ተመልከት። ዝናቡን ማየት ትችላለህ።



*windscreen* ('ዊንድስክሪን)
የመኪና የፊት መስተዋት
The boy broke the windscreen.
ልጁ የመኪናውን የፊት መስተዋት ሰበረው።



*wing* (ዊንግ)
ክንፍ/የወፎች/የአይሮፕላን ወደጎን የተዘረጋ አካል/
Birds use their wings to fly.
ወፎች ለመብረር ክንፎቻቸውን ይጠቀማሉ።

*wink* (ዊንክ)
አይንን ቶሎ ቶሎ መጨፈን መክፈት/መጥቀስ/
When you want me to stop, wink.
እንዳቆም ስትፈልግ ጥቀሰኝ።

*winter* (ዊንተ)
ክረምት/በጣም ቀዝቃዛው የአመቱ ጊዜ/
We wear warm clothes in winter.
በክረምት ሙቀት የሚሰጡ ልብሶችን እንለብሣለን።

*wipe* (ዋይፕ)
በጨርቅ መጥረግ መስታወትን
The window is dirty. Wipe it with a clean cloth.
መስኮቱ ቆሽሿል በንጹህ ወርቅ ጥረገው።

*wire* (ዋየየ)
ሽቦ ቀጭን ብረት/
My father uses wire to make a fence.
አባቴ አጥር ለማጠር ሽቦ ይጠቀማል።



*wise* (ዋይዝ)
ብዙ ነገር የሚያውቅ/ብልህ/ ብልጥ
My uncle is very wise.
አጎቴ በጣም ብልጥ ነው።

*wish* (ዊሽ)
አንድ ነገር እንዲሆን መመኘት
I wish I had a lot of knowledge.
ብዙ እውቀት እንዲኖረኝ እመኛለሁ።

*witch* (ዊች)
ጠንቋይ/ አስማተኛ ሴት
My sister says the old lady is a witch.
እህቴ አሮጊቷን ጠንቋይ ናቸው ትላለች።

*with* (ዊዝ)
ከአንድ ከሌላ ነገር ጋ
I ride a bicycle with my friend.
ከጓደኛዬ ጋር ብስክሌት እነዳለሁ።

*without* (ዊዛውት)
ካለ/አንድ ነገር ሳይዝ/ሳይኖረው
He went home without his school books.
የትምህርት ቤት መጽሃፎቹን ሣይዝ ወደቤቱ ሄደ።

*wizard* (ዊዘድ)
ጠንቋይ/አስማት የሚሰራ ሰው/
Mother says wizards can do magic.
እማዬ ጠንቋዮች አስማት ይሰራሉ ትላለች።

*wolf* (ውልፍ)
ተኩላ/ ውሻ መሳይ የዱር እውሬ
That is a wolf
ያ ተኩላ ነው።



*woman* ('ውመን)
ትልቅ ሴት
That woman is my aunt.
ያቺ ሴት አክስቴ ናት።

*wonderful* ('ወንደፍል)
በጣም ጥሩ/ ደስ የሚል
We went to the city yesterday. It was a wonderful day.
ትላንት ወደ ከተማው ሄደን ነበር። በጣም ደስ የሚል ቀን ነበር።

*wood* (ውድ)
1. ጫካ/ብዙ ዛፎች በአንድነት
They are cutting down some of the trees in the wood.
ከጫካው ውስጥ ጥቂት ዛፎችን እየቆረጡ ነው።
2. እንጨት/ የዛፎች አካል
The tables and chairs are made of wood.
ጠረጴዛውና ወንበሮቹ ከእንጨት የተሠሩ ናቸው።



*wool* (ውል)
የበግ ፀጉር
The sheep look warm with their thick wool.
በጎቹ ከወፍራም ፀጉራቸው ጋር ሲታዩ የሞቃቸው ይመስላል።



*word* (ወ:ድ)
ቃል/ፊደላት ተገጣጥመው የሚፈጥሩት ትርጉም ያለው
Look at the words in that book.
እዛ መጽሃፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ተመልከት።

*work* (ወ:ክ)
ስራ መስራት
My mother works in a bank.
እናቴ ባንክ ቤት ትሠራለች።

*world* (ወ:ልድ)
አለም/መሬትና በላይዋ ላይ ያሉ በሙሉ
I want to go round the world
አለምን መዞር እፈልጋለሁ ።



*worm* (ወ:ም)
ትል/በመሬት ውስጥ የሚኖር ረጅም ቀጭን ነፍሳት/

Worms are useful for soil.
ትላትል ለአፈር ጠቃሚ ናቸው።



*worse* ('ወ:ስ)
በጣም መጥፎ/ቀሽም
Abebe plays tennis worse than I do.
የአበበ ቴኒስ አጨዋወት ከኔ ያነሰ ነው።

*worst* (ወ:ስት)
ከሁሉ የባሰ መጥፎ ቀሽም
Abebe plays tennis worse than I do.
የአበበ ቴኒስ አጨዋወት ከኔ ያነሰ ነው።

*wrap* (ራፕ)
መጠቅለል/መሸፈን
Wrap up the present in the red paper.
ስጦታውን በቀይ ወረቀት ጠቅልለው።

*wreck* (ሬክ)
አደጋ ወይም ግጭት የደረሰበት መኪና/መርከብ
That car is a wreck. Was the driver hurt?
ያ ግጭት የደረሰበት መኪና ነው። ሹፌሩ ተጎድቶ ይሆን?



*wriggle* ('ሪግል)
የተጠማዘዘ/የተጣጠፈ ነገር/ የተጥመለመለ
The road was so wriggle that we got tired.
መንገዱ ጠመዝማዛ ስለነበር ደከመን።

*wrist* (ሪስት)
መዳፍንና ክንድን የሚያገናኝ የሰውነት አካል
He looked at the watch on his wrist.
አምባር መዋያው ላይ ያሰረውን ሰአት ተመለከተ።



*write* (ራይት)
መፃፍ
I am going to write a letter to my brother.
ለወንድሜ ደብዳቤ ልፅፍለት ነው።

*wrong* (ሮንግ)
ትክክል ያልሆነ/ የተሳሳተ
That is the wrong way to school.
ያ መንገድ ወደ ት/ቤት የሚወስደው አይደለም።

*X, x* (ኤክስ)
1. የእንግሊዝኛ 24ኛው ፊደል
2. የስህተት ማሳያ ምልክት


Put the sign X if the sentence is wrong.

ዐረፍተ ነገሩ ስህተት ከሆነ የ X ምልክት አስቀምጥ።

*x- ray* (ኤክስ'ሬይ)
ራጅ/ የሰውነትን ውስጥ የሚያሣይ ፎቶ

You go to a hospital to get an x-ray.


ራጅ ለመነሣት ሆስፒታል መሄድ አለብህ።



# Yy

*Y,y* (ዋይ)
የእንግሊዝኛ 25ኛው ፊደል

*yard* (ያ:ድ)
የተከበበ ቦታ (ለመኪና ማቆሚያ ወይም ለሌላ አገልግሎት)
The farmer put his cattle in the yard.
ገበሬው ከብቶቹን መስኩ ላይ አሰማራቸው።



*yawn* (ዮ:ን)
ማፋሸክ/ማዛጋት/ አፍን መክፈት በድካም
He was so tired after work that he could not stop yawning.
ከስራ በኋላ በጣም ደክሞት ስለነበረ ማዛጋቱን ማቆም አልቻለም።



*year* (ዪየ)
ዓመት 365 1/4 ቀናት
We have been living in this house for one year.
እዚህ ቤት ለአንድ አመት ኖርን።

*yeast* ('ዪ:ስት)
እርሾ
My mother puts yeast in the flour to make bread.
እናቴ ዳቦ ለመጋገር ዱቄቱ ውስጥ እርሾ ጨመረች።

*yell* (ዬል)
መጮህ
The man yelled at the boy to stay away from the fire.
ሰውዬው ልጁን ከእሣቱ እንዲርቅ ጮሆ ነገረው።

*yellow* ('ዬለው)
ቢጫ ቀለም
The bananas are yellow.
ሙዞቹ ቢጫ ናቸው።



*yes*
ኦ ወይም እሺ ወይም ነው ማቁት
I always say 'yes' to my mother.
እኔ ሁልጊዜ ለእናቴ እሺ እላለሁ።


*yesterday* ('ዬስተዲ)
ትላንትና ከዛሬ በፊት የነበረው ቀን
Mother did her washing yesterday.
እናቴ ትላንትና ልብሶቿን አጠበች።

*yet* (ዬት)
ገና/እስከ አሁን
I haven't done my homework yet.
የቤት ስራዬን ገና አልሰራሁም።

*yolk* (የውክ)
የእንቁላል ውስጥ ያለ ቢጫ ክፍል/ አስኳል
The yolk is the middle part of an egg.
አስኳል የእንቁላል መሀከለኛው ክፍል ነው።




*young* (የን)
ወጣት/ገና ያላረጀ እድሜው ትንሽ የሆነ
He is too young to get married.
በጣም ወጣት ስለሆነ ትዳር ለመያዝ ገና ነው።



*youth* (ዩ'ስ)
ወጣትነት
She was a good swimmer in her youth.
በወጣትነቷ ጊዜ ጥሩ ዋናተኛ ነበረች

***Z, z*** ('ዜ:ድ)
የእንግሊዝኛ 26ኛው ፊደል

*zebra* ('ዜ:ብረ)
የሜዳ አህያ/ነጭና ጥቁር ሽንትርትር ፈረስ የመሠለ የዱር እንስሣ
A zebra has black and white stripes.
የሜዳ አህያ ጥቁርና ነጭ መስመሮች አሉት።



*zero* ('ዚየረው)
ዜሮ/ባዶ ምንም/ ከአንድ በፊት ያለ ቁጥር /0/
His work was so bad that the teacher gave him a zero.
የስራው ስራ መጥፎ ስለነበረ መምህሩ መምህሩ ዜሮ ሰጡት።

***zigzag*** ('ዚግዛግ)
የተጣጠፈ መስመር /የተጠማዘዘ/
Look! The road zigzags up the mountain.
ተመልከት መንገዱ ወደ ተራራው እየተጠማዘዘ ወጣ።



*zip* (ዚፕ)
ጃኬት/ሱሪ ላይ የሚሰሩ በቁልፍ ፋንታ ልብስ ማያያዣ
Please zip up my dress.
እባክህ የቀሚሴን ዚፕ ዝጋልኝ።

*zoo* (ዙ:)
የዱር እንስሳት ለእይታ የሚጠበቁበት ቦታ
We are going to the zoo tomorrow.
ነገ ወደ እራዊት መጠበቂያው ሥፍራ እንሄዳለን።

# PARTS OF THE BODY

# የሰውነት ክፍሎች

